# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 205 መጋቢት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# መንግሥት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተደራጀ ሕግ የማስከበር ሥራ ሳይ መሆኑን ገለጸ



ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተደራጀ የሕግ ማስከበር ሥራ እየሠራ መሆኑን የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ኃላፊ ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ የአገሪቱ መንግሥት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተደራጀ የሕግ ማስከበር ሥራ እየሠራ በመሆኑ አብዛኛው የሀገራችን ክፍል አንጻራዊ ሰላም እየሰፈነ ይገኛል ብለዋል።

እየተሠሩ ባሉ የሕግ ማስከበር ሥራዎች በመላው ኦሮሚያ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም እና ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት ለመፍጠር የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል የጸጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት እያሳየ ያለው እንቅስቃሴ የሚበረታታ ነው፡፡ ይህንን በማጎልበት ሁሉንም አካባቢዎች ከሸኔ የሽፍታ ኃይል የማፅዳት ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በአንዳንድ ዞኖች ወረዳዎችና አጎራባች ክልሎች ወሰን አካባቢ የሚንቀሳቀሰው የሸኔ ኃይል እያደረሰ ያለውን የንብረት ዝርፊያ፣ ውድመት፣ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር እና

መንግሥት በሁሉም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ‹‹የግድቡን ቀሪ የግንባታ ተግባራት በውጤታማነት ስመፈጸም የማህበረሰቡ ተሳትፎ እና ድጋፍ ሊጠናከር ይገባል››

**- አቶ ደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ቀሪ የህዳሴ ግድብ የግንባታ ተግባራትን በውጤታማነት ለመፈጸም የሰፊውን ማህበረሰብ ተሳትፎ እና ድጋፍ በተሻለ መንገድ አጠናክሮ

‹‹የግድቡን ቀሪ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

# አስቸኳይ መፍትሔ የሚሻው ከ800 ሚሊየን ብር በላይ ሀብት የባከነበት የሠመራ ስታዲየም

**ወርቁ ማሩ**

በ27 ዓመታቱ የሕወሓት መራሽ ስርዓት ውስጥ የህንጻ በጀትን ሙሉ ለሙሉ ከመዝረፍ ጀምሮ በርካታ የሌብነት ተግባራትን ተመልክተናል፡፡ የሕዝብን ልብ በተስፋ ሞልተው አየር ላይ የቀሩ በርካታ ፕሮጀክቶችንም ታዝበናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ከ16 ቢሊየን ብር በላይ በጀት ተመድቦላቸው በአብዛኛው ሳይጠናቀቁ የቀሩት ስታዲየሞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየው በሀገራችን ካለፉት አስር ዓመታት ወዲህ ተጀምረው በግንባታ ላይ የሚገኙ ከደረጃ አንድ እስከ ሦስት የሚመደቡ 16 ስታዲየሞች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ አብዛኞቹ ግንባታቸው በከፊል ቆሟል።

በዚህ መልኩ ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ከቆሙ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የሠመራ ስታዲየም ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሚዲያ አባላትም በሠመራ

አስቸኳይ መፍትሔ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በጠላት እጅ ሆኖ መፃፍ አይቻልም ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ግን ይህን አድርጎታል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገሩ

**- "የተካደው ሰሜን ዕዝ" መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል**

ገጽ 4









ሼህ ሙሐመድ ጠይብ ሻኪር

## ረመዳንን ስንጾም ተቸግረው በውሃ የሚያፈጥሩትን በመርዳት መሆን አለበት

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ረመዳንን ስንፆም ተቸግረው በውሀ የሚያፈጥሩትን በመርዳት መሆን እንደሚገባ የአዲስ አበባ ኢማሞች ማህበር ፕሬዚዳንት እንዲሁም የላፍቶ ቢላል መስጅድ ዋና ኢማም የሆኑት ሼህ ሙሐመድ ጠይብ ሻኪር ገልጸዋል፡፡

ሼህ ሙሐመድ ጠይብ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በረመዳን ጾም ወቅት የማፍጠርያ ምግብ አማርጠው የሚያፈጥሩ ሰዎች ተቸግረው በውሀ የሚያፈጥሩትን መርዳት መቻል አለባቸው፡፡

የረመዳን ወር በልግስና እንዲሁም መልካም የሆነውን ሁሉ በማድረግ ከፈጣሪ ጋር በመቀራረብ በመመላለስ እንዲሁም የሃይማኖቱን ትዕዛዛት በመፈጸም እንደሚታወቅ የገለጹት ሼህ ሙሐመድ ፤ የጾም ወሩን መልካምን አድርጎ የፈጣሪውን ትዕዛዝ ማሟላት ከማንኛውም ሙስሊም ማህበረሰብ የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የረመዳን ጾም በህዝበ ሙስሊሙ ዘንድ በታላቅ ጉጉት የሚጠበቅ የበረካና የዱአ ወር መሆኑን የገለጹት ሼህ ሙሐመድ፤ ከምንጊዜውም በተለየ መልኩ ሁሉም የእምነቱ ተከታይ ከፈጣሪው በሚገናኝበት በዚህ ወቅት የሚበሉት የሌላቸውን በማብላትና በመርዳት ማሳለፍ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ባላት አሁናዊ ሁኔታ የተለያዩ ሀገሪቷ ነዋሪዎች በችግር ውስጥ እንደሚገኙ የገለጹት ሼህ ሙሐመድ፤ በኑሮ ውድነት ችግር ላይ የወደቁ፣ ጦርነት ለጎዳቸው፣ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን መርዳትና መደገፍ ሰላም ባለባቸው ስፍራዎች ያሉ ሰዎች ኃላፊነት መሆኑን አሳስበዋል፡፡

ሁሉም ሙስሊም በረመዳን ወር ለተቸገረ የሰው ዘር በሙሉ ቁሳዊና መንፈሳዊ እርዳታ ማድረግ እንደሚገባው የገለጹት ሼህ ሙሐመድ፤ ተማሪው በእውቀቱ፣ ነጋዴው በንግዱ፣ የሃይማኖት አባቱ በእምነቱ፣ ሀብታም በንብረቱ ያለውን ሁሉ ለሀገሩ ባለመሰሰት መለገስ እንደሚገባውም ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

የረመዳን ወር ሰላምና አንድነት የሚበዛበት መሆኑን ገልጸው፤ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለሀገሩ ኢትዮጵያ እንዲሁም ለመላው ዓለም ሰላም የሚለምንበትና ሀገሩን በዱዓው የሚያስብበት ሊሆን እንደሚገባውም ገልጸዋል።

ሼህ ሙሐመድ ለመላው የሀገራችን የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉም ለታላቁ የረመዳን ወር የእንኳን አደረሳችሁ መልእክታቸውንም ያስተላለፉ ሲሆን፤ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ቅዱስ ቁርአን በሚያዘው መሰረት የተቸገሩ ሰዎችን ሰደቃ በማብላት አቅሙ በሚፈቅደው መጠን ያለውን በማካፈል፣ ዘካም በመስጠት ይህንን የተቀደሰ ወር በመልካምነት እንዲያሳልፍ ጥሪቸውን አቅርበዋል፡፡

# ግጭት ለማስነሳት የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ክልሉ አሳሰበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ብሄርን ከብሄር፣ እምነትን ከእምነት ለማጋጨት የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል ሲሉ የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ አሳሰቡ፡፡

አቶ ግዛቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጸረ ሰላም ሃይሎች ብሄርና እምነትን መሰረት ያደረገ ግጭት እንዲቀሰቀስ ሙሉ ሃይላቸውን ተጠቅመው እየሰሩ ይገኛሉ። ስርዓት ለማስያዝና ሕግ ለማስከበር የጸጥታ ሃይሉ ስምሪት አድርጓል፡፡

አንዳንድ አካባቢዎች ምልክቶች ይታያሉ፣ የተፈጠሩ ግጭቶችም አሉ፡፡ ጸረ ሰላም ሃይሎች ወትሮም ይሰሩ ነበር አሁን ደግሞ ሙሉ ሃይላቸውን ተጠቅመው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

ችግሩን በሽምግልና እና በተለያዩ የሰላም አማራጮች እያደራደሩ ለማረጋጋት፣ ወደከፋ ግጭት እንዳያድግ እየተሰራ ቢሆንም ሰላምን የማይሹ ሃይሎቹ አሁንም ሊያርፉ አልቻሉም፡፡ በአጎራባች ክልልችም ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች መስተዋላቸውን አንስተዋል፡፡

በማዕከላዊ ጎንደር አካባቢ የቅማንት ጽንፈኛ ቡድን በተደጋጋሚ ትንኮሳ እያደረገ ይገኛል፣ በጃዊ አካባቢም ያለው ዝንባሌ ትክክል አይደለም፣ በተለይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ መተከል ዞን አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ የብሄር ግጭት ለማስነሳት እንቅስቃሴዎች መኖራቸውንና የሰው ሕይወትም እንደጠፉ አስታውሰዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ኦሮሞ ብሄረሰብ ላይ ሰሜን ሸዋ፣ ምንጃር አካባቢም በተመሳሳይ እነዚህ የጥፋት



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ

ሃይሎች ግጭት ለማስነሳት እንቅስቃሴ እያደረጉ ናቸው። ይህ ሕብረተሰብን አይወክልም፡፡ ከሁሉም ብሄሮች ያሉ ሕዝብን ከሕዝብ የማጋጨት፣ የመላላክ ስራና ወደ ሌላ ጽንፍ ለመውሰድ የሚሰሩ አካላት አደብ ሊገዙ ይገባል ብለዋል፡፡

ሰሞኑንም ሰላምን የማወክ ዝንባሌ ይታያል፡፡ በክልሉ ሰላምና ደህንነት ላይ ጠባሳ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ችግሮችም ካሉ መፈታት የሚቻለው በውይይት ብቻ ነው፡፡

ወደ ጦርነት የተገባው የህልውና ስጋት በመኖሩ ነው ያሉት አቶ ግዛቸው፤ አሁንም ሕወሓት በወረራ በያዛቸው አካባቢዎች ላይ የህልውና ስጋት የሆነባቸው አካባቢዎችን መልቀቅ አለበት፡፡ አላማጣ እና ኮረም፣ ዋግ ኽምራ አካባቢም ሶስት ወረዳ ላይ፣ ማይጠብሪ አዲአርቃይ አካባቢዎች ላይም የሽብር ቡድኑ ወረራ ፈጽሟል ብለዋል፡፡

ጠላት በእነዚህ አካባቢዎች ረዘም ያለ ጊዜ እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ዜጎችንም ለእንግልት እየዳረገ ነው፡፡ መንግሥት ባለበት ቆሞ የያዘውን አስጠብቆ ሕዝቡ እፎይታ እንዲያገኝ በሚል እነዚህ አካባቢ ያሉ ሰዎች ዋጋ እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡

መንግሥት የሰላም አማራጭን ቢከተልም ሕወሓት ለእዚህ ዝግጁ የሆነ አይመስልም፡፡ አሸባሪ ሃይሉ ለሰላም ተነሳሽነትን ከማሳየት ይልቅ ለወረራ ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡

ድርጊቱ ቡድኑ ለሕዝብ ደንታ ቢስ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሂደት የሚቀጥል ከሆነ ምን ይሆናል የሚለውን የሚወስነው የፌዴራል መንግሥት ነው፡፡ የፌዴራል መንግሥት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት እንደክልል የድርሻችንን የምንወጣ ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ለዘላቂ ሰላም ትርጉም ከሰጠ በሚል ሕዝብ አላስፈላጊ ዋጋ እየከፈለና እየተንገላታ ይገኛል፡፡ ፌዴራል መንግስትም ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ሕዝብ እየተጎዳ ዝም ማለት ስለማይቻል አንድ ውሳኔ ላይ እንደሚደረስ እንጠብቃለን ብለዋል፡፡

ከጦርነት ይልቅ ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ እንጠብቃለን፡፡ ከዚህም ከዛኛውም ወገን የሚጎዳው ሕዝብ ነው፡፡ ያኛውም የእኛ ሕዝብ እንደመሆኑ እንዲጎዳ አንፈልግም፡፡

መንግስት የሚመራው ፓርቲ ከጉባኤ በኋላ ከህዝብ ጋር ባካሄደው ውይይት የሰላም ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑ ተነስቷል፡፡ ሰላም ለማስፈን መፍትሄዎችና አቅጣጫዎችም ተቀምጠዋል። ሕዝቡን የሰላሙ ባለቤት የማድረግ ጉዳይም የመፍትሄዎቹ አካል መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡



ፎቶ፡ ናሆም አየለ

# ከአጎዋ መሰረዝ የፈጠረውን ስጋት ለመቀነስ እየታዩ ያሉ አማራጭ የገበያ እድሎች

**ፋንታነሽ ክንዴ**

በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከሚገኙ አምራች ኩባንያዎች አንዱ የሴቶች የእጅ ቦርሳ እያመረተ ወደ ውጭ በመላክ ላይ የሚገኘው የፑንግ ኩንግ ፋብሪካ ተጠቃሽ ነው።

ፋብሪካው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራና አፋር ክልሎች በከፈተው ጦርነት ፓርኩ ላይ ውድመት እስካደረሰበት ጊዜ ድረስ አንድ ሺ 16 ሠራተኞች የነበሩት ሲሆን፣ አሁን ላይ 880 የሚሆኑት ሠራተኞች ወደ ሥራ ገበታቸው ተመልሰዋል፡፡

የፋብሪካው የሰው ኃይልና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ አቶ ያሬድ እንዳላማው እንደሚገልጹት፤ ፋብሪካው ከምርቱ 95 በመቶ የሚሆነውን ወደ አሜሪካ ገበያ ሲልክ ቆይቷል፡፡

ፑንግ ኩንግ የሴቶች ቦርሳ አምራች ፋብሪካ በጦርነቱ ምክንያት ከ400 ሺ ዶላር በላይ ጉዳት እንደደረሰበት የሚናገሩት አቶ ያሬድ፤ የምርቱ ዋና ገዢ ማይክል ኮርስ ኩባንያ አሜሪካ ስለሚገኝ ድርጅቱ በጦርነቱ ከደረሰበት ጉዳት ባለፈ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት እንድትወጣ በመደረጉ አዲስ ትዕዛዝ እየተቀበለ አለመሆኑ ስጋት ፈጥሮበታል፡፡

እስካሁን ቀደም ብሎ የተቀበሉትን ትዕዛዝ በማምረት ላይ እንደሚገኙ የሚጠቅሱት ኃላፊው፤ ተጨማሪ ትዕዛዝ ለማግኘትና ምርቱን ለመላክ የሚወጣውን ወጪ መጋራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከገዢው ጋር ድርድር በማድረግ ላይ ነው፡፡ ድርድሩ ውጤት የማያመጣ ከሆነ ግን ድርጅቱ የገበያ እጦት ሊገጥመው እንደሚችል ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የትራይባስ ብሪጅ ቴክስ ኢትዮጵያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አዲሱ ማሞ እንደሚሉት ደግሞ፤ ፋብሪካው ሙሉ ልብሶችን በማምረት ወደ አሜሪካ ገበያ ሲልክ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ተቀብለውት በጦርነቱ ምክንያት የዘገዩ ትዕዛዞችን በማምረት ላይ ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት በመሰረዟ ምክንያት አዲስ ትዕዛዝ እየተቀበሉ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡

በቀጣይነት አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን ለመፈለግ ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን የሚናገሩት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ አውሮፓ ላይ የገበያ እድሎች ቢኖሩም ፋብሪካው በግብዓትነት የሚጠቀማቸው ጥሬ እቃዎች ከውጭ ስለሚመጡ ያለውን ፉክክር ሰብሮ ለመግባት የሚያስችል የዋጋ ተወዳዳሪነት መፍጠር ከባድ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ፋብሪካው በጦርነቱ ምክንያት የ33 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ቀጥተኛ ጉዳት ደርሶበታል የሚሉት አቶ አዲሱ፤ በተጨማሪም ተቀብለውት የነበረው ትዕዛዝ እንደተሰረዘባቸውና ከአንድ ሺ በላይ ሠራተኞችን ለመቅጠር ያስችል የነበረውን የማስፋፊያ ሥራ ለማቆም ተገደዋል፡፡

ፋብሪካው የተቋቋመው ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ በመሆኑ በመንግሥት በኩል መፍትሔዎች ካልተቀመጡ የፋብሪካው ህልውና አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡

የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አሕመድ ሰኢድ እንደሚገልጹት፤ ኢትዮጵያ ከኮታ እና ቀረጥ ነጻ የገበያ እድል ወይም አጎዋ ተጠቃሚነት መሰረዟን ተከትሎ የተፈጠረውን የምርት መዳረሻ ገበያ ማጣት ስጋትን ለመፍታት አማራጭ የገበያ እድሎች እየተፈለገ ነው፡፡

አብዛኞቹ የፓርኩ ባለሀብቶች ምርታቸውን በብዛት የሚልኩት ወደ አሜሪካና አውሮፓ አገራት በመሆኑ የኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት መታገድ በአምራቾች ላይ ችግር ፈጥሯል የሚሉት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በኩል አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ለሦስት ሳምንት ያህል ዱባይ ኤክስፖ ላይ መሳተፋቸውን ያነሱት አቶ አሕመድ፤ በቆይታቸውም ከዱባይ ባለሀብቶች ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከዋና መሥሪያ ቤቱ የተወከለ ቡድን የገበያ አማራጮችን ለማየት ወደ ሕንድ ማምራቱንም ያስረዳሉ፡፡

አማራጮችን ለመፈለግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ተከትሎ በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙ ካምፓኒዎች በሙከራ ጀረጃ ምርቶችን ወደ አውሮፓ ለመላክ አማራጭ የሙከራ ምርቶችን እየሠሩ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ረመዳንን በፍቅር በአንድነትና በመተሳሰብ!

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ፈተናዎችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች፡፡ በአንድ በኩል የውጭ ጠላቶቻችን ሃገራችንን ለማፍረስ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩበትና ዛሬም የቀጠሉበት ወቅት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣዊ ችግሮቻችንም በርካታ ፈተናዎችን እያስተናገድን ያለንበት ወቅት ነው፡፡

በውጭ ያሉ ጫናዎችን ስንመለከት በተለይ ከታሪካዊ ማንነታችን እና ከነፃነታችን ጋር የተገናኘውን የቆየ ማንነታችንን የሚፈታተን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ያላትን የረጅም ጊዜ የነፃነት እና የሉአላዊነት ታሪክ የማይፈልጉና ዛሬም እነሱ በሚፈልጉት መልኩ በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ እንደፈለጉ ለማሽከርከር የሚፈልጉ ኃይሎች በኛ መንገድ ካልሄዳችሁ እናፈርሳችኋለን በሚል በተለያዩ መንገዶች ጫናዎችን እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡

በተለይ ለሃገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት መሰረታዊ ለውጥ እንደሚመጣ የሚጠበቀውን የታላቁ ህዳሴ ግድብን በራሳችን አቅምና ገንዘብ ጀምረን ኃይል እስከማምረት ድረስ መዝለቃችን ያልተዋጠላቸው የውጭ ጠላቶች ይህንን ስራችንን ለማደናቀፍ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፡፡ አንዴ ፀጥታው ምክር ቤት፤ ሌላ ጊዜ በግብረሰናይ ድርጅቶች ስም፤ እንዲሁም በሚዲያዎቻቸውም ጭምር ሲፈታተኑን ከርመዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ጫናዎች ከጀመርነው የለውጥ መንገድ ሊያስቆሙን አልቻሉም፡፡

ሃገራችን ሳትወድ በግድ ተገዳ የገባችበትን ጦርነት ሌላ ገጽታ በማላበስ እና በዴሞክራሲና ሰብአዊ ድጋፍ ስም ጣልቃ በመግባት በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ከፍተኛ ርብርብ ሲያደርጉ ሰንብተዋል፡፡ ሰሞኑን ደግሞ ኤችአር6600 እና ኤስ3199 የሚሉ ጎጂ ህጎችን ተግባራዊ በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር ከፍተኛ ርብርብ ሲደረግ እያስተዋልን ነው፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ አዲሱን የለውጥ መንገድ ለመጀመር መንቀሳቀስ ከጀመረችበት ዋዜማ ጀምሮ በአሸባሪው ሕወሓት አማካኝነት በርካታ ፈተናዎች ደርሰዋል፡፡ ይህ ቡድን በተለይ የለውጡን እውን መሆን ተከትሎ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ግጭቶችን ስፖንሰር በማድረግና አንዱን ህዝብ ከሌላው ህዝብ ጋር በማጋጨት ሀገር ለማፍረስ በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል።

በተለይ በሃገሪቱ ውስጥ በታሪክም ሆነ በማህበራዊ ኑሮአቸው ከፍተኛ ትስስር ያላቸውን የአማራና ኦሮሞ ማህበረሰብ ክፍሎች ለማጋጨትና ሀገሪቱን ለመበተን ያልተሞከረ ትንኮሳ የለም፡፡ እስከዛሬም ድረስ በነዚህ ሁለት ትላልቅ የሃገሪቱ ህዝቦች ላይ የሚደረገው ተንኮልና ሴራ ከፍተኛ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሃገራችን በተለይ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ሕዝብና ሕዝብን ለማጋጨት በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ በተለይ አሸባሪው ሕወሓት ተስፋ በቆረጠ ጊዜ በተለያዩ አካባቢዎች አንዴ ቤተክርስያናትን፤ ሌላ ጊዜ መስጊዶችን በማቃጠል ሁለቱን የእምነት ተቋማትና አማኞች ለማጋጨት በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት እምነቶች ለብዙ ሺህ ዓመታት አብረው የኖሩ ብቻ ሳይሆን አንዱ ለሌላው በመቆርቆርና አብሮነትን በማጠናከር እርስ በርሳቸው ተዋደውና ተከባብረው የኖሩ በመሆናቸው የሴረኞች መጠቀሚያ መሆን አልቻሉም፡፡ ይልቁንም ህዝበ ሙስሊሙም ሆነ ህዝብ ክርስቲያኑ እነዚህን ሴራዎች በንቃት በመከታተልና ችግሮችን በጋራ በመፍታት የሴረኞችን ክፉ ተግባር በመቅጨት የታለመው የጠላት ሴራ እንዳይሳካ ማድረግ ችለዋል፡፡

በሌላ በኩል አሸባሪው ሕወሓት በተለያዩ የአማራና የአፋር ክልሎች ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱ አልቀረም፡፡ በዚህም በነዚህ አካባቢዎች በብዙ ቢሊየን የሚገመት ንብረት ወድሟል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችም ተፈናቅለዋል፡፡ የተፈናቀሉ ዜጎች እና የወደመውን ንብረት ለመተካት ደግሞ ገና ብዙ ጥረት ይጠይቃል፡፡

እነዚህ ዜጎች በተለይ ታላቁን የረመዳን ወር በዚህ መልኩ ከቤታቸው ውጪ ሲያሳልፉ ከባድ ፈተናን እየተጋፈጡ እንደሆነ አይካድም፡፡ በታላቁ የረመዳን ፆም ቀርቶ በሌላ ጊዜም ቢሆን ከቤት መፈናቀል የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው። ከማጀታቸው የሚጎድል በርካታ ነገር ይኖራል፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ የወንድሞቻቸውን እና የእህቶቻቸውን ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈልጉበት ወቅት ነው፡፡

ከነዚህ ሰው ሰራሽ ፈተናዎች በተጨማሪ ደግሞ በተለይ ካለፈው አመት ጀምሮ በሶማሌና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ በርካታ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮችን ለጉዳት ዳርጓል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች በርካታ የቤት እንስሳት አልቀዋል፤ ዜጎችም ለከፍተኛ ችግር ተዳርገዋል፡፡ በመሆኑም በፆም ወቅት የረመዳን መርህ የሆኑትን መተሳሰብ መተዛዘንና አንድነትን በማጽናት በችግር ላይ ያሉትን ዜጎችን ማሰብና የሚቻለውን ያህል ድጋፍ ማድረግ ከእያንዳንዱ ህዝበ ሙስሊም የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ረመዳን የበጎ ነገሮች ሁሉ ወር በመሆኑ ይቅርታ የሚያብብበት ፣ ሰላምና መተሳሰብ የሚጎለብትበት ፣ ስለሃገራችን ስለህዝባችን የሚፀለይበት ፣ አንድነታችን የሚጠነክርበት ፣ የደከሙት የሚደገፉበት ፣ ያዘኑት የሚፅናኑበት ፣ ካለን የምናካፍልበት ፣ የታረዙት የሚለብሱበት ፣ ማዕዳችንን የምናቋድስበት ፣ በረከቱ ለብዙዎች የሚደርስበት በመሆኑ ይህንን ወር እነዚህን የተቸገሩ ወገኖቻችንን በመደገፍ እና በጎ ተግባራትን በመስራት ልናሳልፈው ይገባል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በጊዜው ሲሆን የሚገባው የፌስቡክ መርዘኞች ማርከሻ

**ታምራት ተስፋዬ**

በአሁኑ ወቅት በፌስቡኩ መንደር መልካም እና ገንቢ እሳቤዎች የሚንሸራሸሩበትን ያህል በብዙ መልኩ የስነ ስርዓትና የስነ ምግባር ዝቅጠት ጎልቶና ተደጋግሞ ይታያል። በርካቶችም ጥላቻንና ስሜታዊነትን የሚሰብኩበት፤ ጦርነት የሚቀሰቅሱበት፤ ግለሰብን፣ ህዝብና አገርን የሚዘልፉና የሚያፈርሱ መልእክቶችን የሚያስተላልፉበት ሲሆን እያስተዋልን እንገኛለን፡፡ መንደሩም «ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት» በሚል የህግ ሽፋን ድብቅ አላማ ባነገቡ እና መርዛም ብዕር በጨበጡ ፀሃፍት ተወሯል፡፡

እኔ እንደታዘበኩት የእነዚህ መርዛም ፀሃፍት የአንድነት መገለጫ ብዙ ነው። ጥላቻ እንጂ ፍቅር አያውቁም። ሞት እንጂ ህይወትን አይመርጡም።ጥፋት እንጂ ልማት ዓላማቸው አይደለም። ከማዳን ለመቅበር ይቸኩላሉ። አዕምሯቸው በመንደር ማንነት የታጠረ ነው።አያስቡም።አይጨነቁም። አበጥሮ ከማጣራት በሩቁና በግርድፉ መፈረጅ ይቀላቸዋል። አንድን ክስተት በርዝውና ከልሰው እንዳልሆነ ያሰፍራሉ። የድብቅብቆሽ ዓለምን እየፈጠሩ የጠራውን ከደፈረሰው፣ የፀዳውን ካደፈው ይደባልቃሉ።

በስሜተኛነትና በወገንተኛነት የተበከሉ በመሆናቸው የጠራውንና የነጣውን እውነት ከጎደፈ የግል አስተያየት ጋር አጋብተው ያቀርቡታል።እውነትን በውሸት ይለውሳሉ። ያታልላሉ፡፡ ማሰብ መጨነቅን፣ማበጠር ማጣራትን አያውቁም።የሚዘሩት ጥላቻ፣ የሚያቆሙት ሐውልት፣ የሚያፈርሱት ምልክት፣ የሚጽፉት ከታብ፣ የሚያበጁት ገደብ፣ የሚቆፍሩት ጉድጓድ እጅጉን አስፈሪ ነው፡፡

አብዛኞቹ ፍርሃትንና ስጋትን በማሰራጨት ህዝብን ምቾትና እንቅልፍ ማሳጣት ዓላማቸው ያደረጉ የጥፋት ጥቅመኞች ናቸው። በኢትዮጵያ እኩልነት ዴሞክራሲ ነፃነትና ፍትህ እንዲሰፍን ፍላጎት የላቸውም።በአገሪቱ የተጀመረው ሁለንተናዊ ለውጥ ቀጣይ እንዳይሆን የሚችሉትን ሁሉ ያዋጣሉ፡፡

በህዝብ ስቃይ የሚንፈነድቁ የእነዚህ ፀሃፍት የጥፋት ተግባር መነሾ የሚቀዳውም ጥልቅ ከሆነው የግል ጠብና ቂማቸው ነው። በዚህ የተስፋ ቢስነት ጥላቻና ቂም የተዋቀሩ እንደመሆናቸውም በመርዛማ ብዕራቸው የሚረጩት መርዝ አደገኛነት አይረዱትም።

ከሁሉ በላይ አንድ የሚያደርጋቸው መገለጫም የተቃራኒ ምኞት ሰለባ መሆናቸው ነው። እነዚህ ፀሃፍት ከየራሳቸው ምኞት ውጭ የሚያዩት የለም። ከአስደሳቹ ይልቅ የሚያስለቅሰውን መራጮች ናቸው። አምጠው የወለዱት ክፋት ለማሳደግ የሚሞክሩ፤ ክፋታቸው ተመልሶ እነሱን እንደሚያቃጥል እንኳን በቅጡ የማይገነዘቡ ድኩማን ናቸው።

የሆነውንም፤ያልሆነውም፤ ቢያውቁትም ሆነ ባያውቁት የመጣላቸውን ሁሉ መዘርገፍ ምርጫቸው ነው። የማሳወቅ እንጂ የማወቅ አምሮት የላቸውም። ለማስተማር መማር እንደሚያስፈልግ የዘነጉ፤ ለማሳወቅ ማወቅ ግድ እንደሚል የማይረዱ ናቸው።

ከመገንባት ይልቅ ማፍረስ ይቀናቸዋል። ከመፍጠር ይልቅ አቃቂር ማውጣት ምርጫቸው ነው። የተሻለ ካስተዋሉም ለማኮሰስ ወይም ለማሳነስ ይጣጣራሉ። በጎሳ ምሽጉ ውስጥ የገቡ በመሆናቸው አንድነት ውስጥ ልዩነትን ለማጉላት ይማማላሉ። አእምሮአቸው ውስጥ ባስቀመጡት ምስል በጅምላ ይጠላሉ፤ ይንቃሉ፤ ይሰድባሉ፤ ያዋርዳሉ።

ከመንቀፍም ባለፈ ለወደፊት የሚሻሻልበትን ምክር መስጠት ምርጫቸው አይደለም። በማንኛውም ርእሰ ጉዳይ ወይም አጀንዳ ላይ ማጠቃለያ ለመስጠት ይቸኩላሉ። ማጠቃለያቸውም ከስሜት የመነጨ እንጂ ትክክለኛ አመክኒዮን መሰረት አድርጎ የሚቀመር አይደለም።

ሊኖራቸው ቢገባም ራሳቸውን የመውቀስ ባህል የላቸውም። ሁልጊዜ ትክክል መሆን ስለሚፈልጉ ስህተትን መቀበል እሬት እሬት ይላቸዋል። ስህተትን መቀበል ቀርቶ ከነአካቴው ስህተቱ አይታያቸውም።ስህተትን ከመቀበል ይልቅ ወደ ሌሎች ለማላከክ የሚሽቀዳደሙ ናቸው።

ህዝብ ተረጋግቶ እንዳይኖር የተሳሳተ ዓላማቸውን በሰው አእምሮ ውስጥ የሚያሰርፁት እነዚህ በሶሻል ሚድያው የፈሰሱ የፌስቡክ ፀሃፍት ሌላ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር አብዛኞቹ ማንነታቸውን በፎቶ አለመግለፃቸው ነው። እነ ስሙ ሌላ መልኩ ሌላ ናቸው።

ምንም እንኳን ትክክለኛ ፎቶአቸውን በማስቀመጥ ማንነታቸውን ሳይድበቁ መርዝ የሚረጩት ቁጥር በርካታ ቢሆን አብዛኞቹ ግን ማንነታቸውን አያሳውቁም።ፎቶአቸውን አያስቀምጡም። አንዳንዶችም የግለሰቦችንና የድርጅቶችን ተመሳሳይ ስም ይጠቀማሉ። ይህ መሆኑም ያሻቸውን በፈለጉት መንገድ ለማስተላለፍ ከለላን ሰጥቷቸዋል። የሚያከብሩት ሕግ፣ የሚፈሩት ኃይል እንዳይኖር አድርጓቸዋል።

ማንነታቸውን ደብቀው ራሳቸውን በተለያየ ማንነት የሚያስተዋውቁ እነዚህ ስመ ብዙ መርዛማ ፀሃፍት፤ በዚህ ጭንብል ተሸፍነው ወተቱን አጥቁረው፤ ማሩን አምርረው ይቀርባሉ። ሰዎችን ከሰዋዊ ክብራቸው ዝቅ ያደርጋሉ። ያዋርዳሉ። «ትንሽ ምላጭ አገር ትላጭ»እንደሚባለው በመሰል የወረደ ተግባር በርካቶችን መርዘዋል፣ እየመረዙም ናቸው፡፡

በጣም የሚያሳዝነውና ሚያስገርመው ደግሞ ፀሃፍቶቹ በርካታ መርዝ አከፋፋይ ማለትም ሼር አድራጊዎች አሏቸው። ከመንቀፍ ይልቅ ጎበዝ! በርታ! የሚሏቸውና መርዙን መውደዳቸውን‹‹ላይክ›› በማድረግ የሚገልፁ ተከታዮቻቸው ቁጥርም በርካታ ነው።

ይሁንና በእነዚህ መርዛም ብዕር የጨበጡ ፀሃፍትና አከፋፋዮቻቸው በርካታ ንፁሃን እየተጎዱ ነው።ብሄር፣ ፆታና ቦታ በመቀየር የግጭት ድግስ የሚደግሱ ግጭት በመቀስቀስና ብጥብጥ በማንገስ የህዝብ መፈናቀልና ስቃይን እያባባሱት ይገኛሉ።

በተለይ የፀሃፍቶቹን ድብቅ ዓላማ ያልተረዱ ንፁሃን ወገኖች ሳያጣሩ በሚሰጡት አፀፋ ህዝቦች ወደ ግጭት ሲያመሩና ሲተናኮሱ እያስተዋልንም እንገኛለን። በአሁኑ ወቅትም መርዝ የሚያሰራጩ ፀሃፍቶቹ ቁጥርም ሆነ በእነርሱ ተግባር የሚደርሱ ጥፋቶች እየጨመሩ እንጂ እየቀነሰ አይደለም። ይህ እስከሆነም ጠንሳሾቹ ሳይውል ሳያድር ከመንደሩ ሊሸሹ የሚችሉበት መፍትሄ መቀየስ የነገ ሳይሆን የዛሬ ተግባር ሊሆን የግድ እንደሚል ማሰብ ይኖርብናል።

በእርግጥ የሰው ልጅ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ እንዲሁም መረጃን የማግኘት መብቱ እንዳለው አያከራክርም፡፡ በዲሞክራሲያዊ አገር መሰል መብቶች መገደብ እንደሌለባቸውም ሁላችንንም ያስማማል፡፡ በአገር ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ምክንያታዊና ተጨባጭ በሆነ መልኩ የሚሰጡ ገንቢ ሃሳቦችና በመንግስት አሰራር ላይ በሚታዩ ድክመቶች ዙሪያ የሚሰጡ አስተያየቶችና ትችቶች መበራከታቸውም የሚጠላ አይደለም፡፡ አስተማሪና ለለውጥ መነሾ ሊሆኑ እንደሚችሉም ጥርጥር የለውም፡፡

ይሁንና በሰንካላ አስተሳሰብና በተንኮል በህዝቦች መካከል መርዝ መርጨትን እንደመብት ወይም ሃሳብን በነፃነት እንደመግለፅ መመልከት ነገ እንባና ደም ወለዱን ጨምሮ እንደሚያስከፍል መገንዘብ የግድ ነው፡፡ መሰል አካሄድም ሳይውል ሳያድርም በቃ ሊባል እንደሚገባው በእጅጉ መተማመን ይኖርብናል።

የፌስቡኩን መንደር የወረሩትን መርዝ የሚረጩት ብዕረኞች ዓላማ ለማክሸፍ ደግሞ ቀዳሚው የተጠቃሚው ሃላፊነት ነው። ከሁሉ ቀድሞም ለፀሃፍቶቹ ድጋፍ መቸር የአእምሮንና የኅሊናን መዳከም ወይም ጭራሹኑ አለመኖር እንደሚያመላክት መረዳት ይገባል።

እንደ ፀሃፍቶቹ ላለመጥበብና በራስ የአስተሳሰብ ሳጥን ብቻ ላለመታጠርም ጥበብ ያለው ማንበብን መልመድ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ጥበብ የሌለው ማንበብ ትክክለኛና የተመጣጠነ አስተሳሰብ እንዲሁም አስተዋይ አዕምሮን አይገነባምና ነው።

የፀሃፍቶቹ ዓላማ ህዝብንና አገርን ምቾት እንቅልፍ ማሳጣት መሆኑን ከመገንዘብ ስህተታቸውን አይቶ ከማለፍ ይልቅም «ስህተቱን ነው ፣ ቀጣፊ ናችሁ» ማለትና በተጨባጭ ምክንያት ብሎም ማስረጃ መሟገትን ልምድ ማድረግም ያስፈልጋል።

መርዛም ብዕረኞችም ቢሆን አንድን ክስተት በርዝውና ከልሰው የጠራውን ከደፈረሰው፣ የፀዳውን ከአደፈው መደባለቃቸውና፤ መልዕክታቸው በብዙ ሰዎች ስለ ተደገፈ እውነት አይሆንምና ሁልጊዜም ቢሆን ምክንያትን ማስቀደም፣ መረጃዎችን እየመረጡ ለመጠቀምና መመርመር ሊያስቡ ይገባል።

የፌስቡኩን መንደር የወረሩትን መርዝ የሚረጩት ብዕረኞች ዓላማ ለማክሸፍ መንግሥትም ቢሆን ኃላፊነቱ ግዙፍ ነው፡፡ በርካታ አገራት አፍሪካዊቷ ግብፅን ጨምሮ በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁ ሀሰተኛ መረጃዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ህግ አውጥተዋል። እኛም በተደጋጋሚ የቀውሱ ገፈት ቀማሽ በመሆናችን በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ያለውን የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ በአግባቡ መጠቀም፤ ካልሆነም አጠናክሮ ማውጣት ይገባል። ይህ ሲሆን ነው የማህበራዊ ሚዲያው መርዘኞች ዘላቂ ማርከሻ የሚያገኙት፡፡

ዜና

# በጠላት እጅ ሆኖ መፃፍ አይቻልም ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ግን ይህን አድርጎታል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገሩ

## - "የተካደው ሰሜን ዕዝ" መጽሐፍ ስንባብ በቅቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ማንም ደራሲ በጠላት እጅ ሆኖ መፃፍ አይችልም "የተካደው ሰሜን ዕዝ" መጽሐፍ ደራሲ ግን ይህን አድርጎታል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገሩ።

በሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው የተጻፈው "የተካደው ሰሜን ዕዝ " የታፈነው ወጥቶ አደር ማስታወሻ የተሰኘው መጽሐፍ ትናንትና በብሔራዊ ቴአትር ተመርቋል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በመጽሐፉ ምረቃ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ ማንም ደራሲ በጠላት እጅ ሆኖ መፃፍ አይችልም፤ ይህን ግን ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው አድርጎታል ሲሉ ደራሲውን አሞካሽተዋል።

በዚያ የጭንቅ ጊዜ ሠራዊቱ በትግራይ ክልል አፈና ውስጥ በነበረበት ወቅት የሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ማስታወሻ መያዙ የሚደንቅ ነው ብለዋል።

የተካደው ሰሜን ዕዝ መጽሐፍ የደራሲው የግል ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ታሪክ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ በአይኑ ያየውንና የሰማውን በግሩም ቋንቋ ተርኮታል ሲሉ ተናግረዋል።

ደራሲው የተባ ብዕር ያነሳ፤ ዕውነትን በሚደንቅ መንገድ የሚተርክ ጸሐፊ ነው ሲሉ አሞካሽተውታል።

በዚህ ደረጃ ታሪክን የሚሰንዱ ሰዎች ሲገኙ ከጸሐፊዎቹ ይልቅ አንባብያኑ ዕድለኞች ናቸው ብለዋል።

በዓለም በርካታ ድንቅ መጽሐፍት የወጡት ከወታደር ቤት ነው ያሉት ዶክተር ዐብይ፤ ከወታደር ቤት የተገኘው ደራሲውም ይህን አይነት የጽሁፍ ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉ ምክር ለግሰዋል።

ወታደር እራሱን በሚያውቀው ልክ ጠላቱን ካላወቀ አያሸንፍም፤ አለማወቅ፤ መናቅና ማናናቅ ምን ያክል ጣጣ እንዳለው የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤




ጠላቶቻችን በታሪክም ከውጭ መምታትና ከውስጥ መከፋፈልን ያቅዱልናል። ወጥተን አንድ መሆን አለብን ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

መጽሐፉን ያዘጋጁት ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው የሰሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊት አባል ናቸው። ጥቅምት 24 ቀን 2013 በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ሲፈጸም በሕወሓት ታጣቂዎች "ታፍነው" ተወስደው የነበሩ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በእገታ ያሳለፏቸውን ጊዜያትና ገጠመኞቻቸውን ይተርካል።

ደራሲው ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ መጽሐፉን እንዳዘጋጀ በምሽግ ሆነው ለተዋደቁ ጓዶቼ ምስጋና ይገባል ብለዋል።

ደራሲው ከዚህ ቀደም "ውሽታም" የተሰኘ የግጥም መድብልና "በሠራዊቱ ውስጥ የነበረውን ብልሹ አሰራር" በልብ ወለድ መልክ ያቀረቡበትን "ኢትዮጵያ ትሙት" የተሰኙ መጽሐፍትን ለአንባብያን አበርክተዋል።

"የተካደው ሰሜን ዕዝ" መጽሐፍ ምረቃ ላይ ብርጋዴር ጄነራል ካሳዬ ጨመዳ፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትና ሌሎች ታዋቂ ሰዎችም ተገኝተዋል።

# መንግሥት በሁሉም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መፈናቀልን የክልልና የፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች በተቀናጀ እና ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ከፍተኛ የተባለ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

እስካሁን በተደረገ ኦፕሬሽንም በርካታ የሸኔ አባላት መደምሰሳቸውን እና የስንቅና የመሣሪያ አቅርቦት ሆነው ይሠሩ የነበሩ አካባቢዎችም ከሸኔ እየጸዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተወሰደው እርምጃ ህብረተሰቡ ያሳየው አጋርነት በጣም የሚያስመሰግን እንደሆነ የገለጹት ኃላፊ ሚኒስትሩ፤ ተታለው ወደዚህ አስጸያፊ ተግባር የገቡ የሽፍታው ቡድን አባላት በአባ ገዳዎችና በሀገር ሽማግሌዎች ምክር በርካታ ታጣቂዎች እጃቸውን እየሰጡ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት በመላ ሀገሪቱ ሕግና ሥርዓት ለማስከበር እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል አንጻራዊ ሰላም እየሰፈነ ቢገኝም፤ የተለያዩ መዋጮዎችን በግዴታ የሚያስከፍሉ፣ ሕፃናትን በማፈን መደራደሪያ የሚያደርጉ፣ ሴቶችን አስገድደው የሚደፍሩ፣ የመንግሥትን ሥራ የሚያደናቅፉ፣ በንጹሃን ዜጎችና በጸጥታ ኃይሎች ላይ ድንገተኛ ጥቃት የሚፈጽሙ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች እየተለመዱ መጥተዋል፡፡ በዚህም ሕብረተሰቡ እየተንገላታ በመሆኑ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በመንግሥት የተደራጀ ሕግ የማስከበር የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ እንደገባ ገልጸዋል፡፡

በተያያዘ የሕወሓት ታጣቂዎች በጉልበት ከያዟቸው የአፋርና የአማራ አካባቢዎች በመውጣት ህብረተሰቡ ከቀየው ሳይፈናቀል ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የጠቀሱት ዶክተር ለገሰ፤ መንግሥት በገባው ቃል መሠረት ውሳኔው ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የሰብዓዊ ዕርዳታው በየብስና በአየር ትራንስፖርት እንዲጓጓዝ አፋጣኝ ምላሽ ሰጥቷል ብለዋል፡፡

በዚህም መሠረት የዓለም አቀፍ ረጂ ተቋማት መድኃኒቶችን፣ የህክምና ቁሳቁሶችን አልሚ ምግቦችንና ሌሎች ሰብዓዊ ድጋፎችን በተመቻቸላቸው የየዕለት የአየር ትራንስፖርት በቻሉት መጠን ማጓጓዝ ጀምረዋል ብለዋል።

በየብስ ትራንስፖርትም በአብአላ መንገድ በዓለም ምግብ ድርጅት አቅራቢነት ዕርዳታዎችን ማጓጓዝ እንደተጀመረና በመጀመሪያው ዙር በዓለም ምግብ ድርጅት ዕርዳታ አቅራቢነት ከተላኩት 20 ከባድ ተሽከርካሪዎች 13 ያህሉ መቀሌ እንደገቡ በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

የአፋር ሕዝብና መንግሥት የሕወሓት ታጣቂዎች የሚያደርሱትን ግፍና ግድያ ተቋቁመው በትግራይ ክልል ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ያሉ እህትና ወንድሞቹን ለመታደግ ያሳየው ትብብርና በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ያሳዩት ዝግጁነት በእጅጉ የሚያስመሰግናቸው ነው ብለዋል፡፡

የሕወሓት ታጣቂዎች በጉልበት ከያዟቸው አካባቢዎች አለመውጣታቸውን ተከትሎ ለሰብዓዊነት የቆመ ሁሉ ግፊት እንዲያደረግባቸው መንግሥት ጥሪውን አቅርቧል፡፡

አገልግሎቱ የኢኮኖሚ መረጋጋትና የዋጋ ንረትን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫም መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ዕቅድ አውጥቶ ወደሥራ መግባቱ ተጠቅሷል፡፡

ለዋጋ ንረትና ግሽበት ዓለም አቀፍ የሆኑና ሀገራዊ የሆኑ ምክንያቶች እንዳሉት ተጠቅሷል፡፡ የዓለም አቀፍ ሸቀጦች ዋጋ መናር፤ በሸማቾችና በአምራቾች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለመኖር እና ከመሠረታዊ ፍላጎታችን ጋር የሚመጣጠን ምርትና ምርታማነት አለመኖር ለዋጋ ንረትና ለኑሮ ውድነቱ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ተብለዋል፡፡

እነዚህን ችግሮች የወለዱትን የዋጋ መናርና የኑሮ ውድነት ህብረተሰቡን ጭምር በማሳተፍ መንግሥት በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ለመፍታት ዕቅድ አውጥቶ ወደ ሥራ እንደገባ መግለጫው አትቷል፡፡

በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን አሻጥር ለመቅረፍ ከተለያዩ ሕግ አስከባሪ አካላት እና ተቋማት የተውጣጣ ግብረ ኃይል ተደራጅቶ በየደረጃው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሕግና ሥርዓት የማስከበር ሥራ እንደተጀመረ ዶክተር ለገሰ ገልጸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለዋጋ መናር አስተዋፅዖ አድርገዋል በተባሉ የንግድ ድርጅቶች ላይ እርምጃ መውሰድ ተጀምሯል፡፡

መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን በመጋዘን በመከዘን፣ በማሸሽ፣ በኮንትሮባንድ ወደውጪ ሀገር ለማውጣት የአቅርቦት እጥረት ለመፍጠር በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃዎችን መውሰድ እንደተጀመረና ከነዚህ አካላት ጋር ትስስር ያላቸውና በመንግሥት ተቋማት በሚሠሩትም ላይ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑ ተነግሯል፡፡

ይህ ቁጥጥርና ሕግና ሥርዓት የማስከበር ጉዳይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልጿል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል የተፈጸሙ ግዢዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር ውስጥ በፍጥነት እንዲጓጓዙ እና ከፍላጎቱ ጋር ሊመጣጠን የሚችል ተጨማሪ ፈጣን ግዢዎች እንዲፈጸሙ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

# አስቸኳይ መፍትሔ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቆይታችን ይህ ስታዲየም በአሁኑ ወቅት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን ለመመልከት ወደስታዲየሙ ጎራ ብለን ነበር፡፡ ወደስፍራው ስንደርስ የተመለከትነው ግን የህንጻ ክምር እንጂ እንቅስቃሴ የሚታይበት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አልነበረም፡፡

በስታዲየሙ ዙሪያ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ ታስበው የተገነቡት ያላለቁ ክፍሎች መስታወቶች ረግፈው እና ህንጻውም ተሰነጣጥቆ ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአካባቢው ላይ ያለው የተረፈ ግንባታ እቃዎችና የመስተዋት ስብርባሪዎች አካባቢውን በጦርነት የፈረሰ መንደር አስመስለውታል፡፡

በዙሪያው ያሉት በሮችም ክፍት በመሆናቸውና ጥበቃም ባለመኖሩ በአንዱ በር ወደውስጥ ዘለቅን፡፡ በስታዲየሙ ሜዳ ላይ በጎች ደረቁን ሳር ሲግጡ፤ በተመልካች ቦታው ላይ ደግሞ ፍየሎች ያገኙትን የወዳደቁ ነገሮች ሲለቃቅሙ ተመለከትን፡፡

የስታዲየሙ ሜዳ ቀደም ሲል ሳር ተነጥፎበት እንደነበር ከደረቀው ሳር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር በሜዳው ዙሪያ ያለው የመሮጫ መም የተጠናቀቀ ቢሆንም በእንክብካቤ እጦት የተነሳ በመበላሸት ላይ ነው፡፡

እኛም አናውን ስታዲየም ተመልክተን በአቅራቢያው ወደሚገኘው የሠመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጎራ ስንል በትምህርት ቤቱ በሚገኘው የአቧራ ሜዳ ላይ ታዳጊዎች አቧራ ለብሰው ልምምድ ሲሰሩ ተመልክተን አሰልጣኙን ጠየቅን፡፡

ወጣት አብደላ ሃቲ ይባላል፡፡ በአፋር ከ15 ዓመት በታች ፓይለት ፕሮጀክት አሰልጣኝ ነው፡፡

ወጣት አብደላ እንደሚለው አፋር ከፍተኛ ሙቀት ያለበት ስፍራ በመሆኑ ከታች ጀምሮ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራበት እና የብሄራዊ ቡድኑ ተጫዋቾችም ልምምዳቸውን እዚህ ቢያደርጉ ውጤታማ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾችን ማፍራት ይቻላል፡፡ በተለይ ሞቃታማ አካባቢዎች ካላቸው ሃገራት ጋር ለሚኖር ግጥሚያ እዚህ አካባቢ ልምምድ ቢደረግ ለውጤታማነት ጠቃሚ ነው፡፡ ነገር ግን ስታዲየሙ ከጅምሩ ጀምሮ ስፖርትን ታሳቢ አድርጎ ባለመጀመሩ በዚህ መልኩ ቆሞ ቀርቷል፡፡ ይህ ደግሞ ለሀገራችንም ሆነ ለክልላችን ኪሳራ ነው፡፡

እንዲህ አይነት ስታዲየም እያለ ልጆች አቧራ ላይ መጫወታቸው አሳዛኝ ነው የሚለው ወጣት አብደላ፣ ስታዲየሙ ለክልሉ የስፖርት እድገት ጠቃሚ በመሆኑ ቶሎ ተጠናቆ ወደስራ ቢገባ መልካም ነው ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

በ2009 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የግንባታ ስራው የተጀመረው ሠመራ ስታዲየም መጀመሪያ አካባቢ የነበረው አፈጻጸም ከፍተኛ እንደነበር ግንባታውን በባለቤትነት የሚከታተለው የክልሉ የዲዛይን፣ ግንባታና ውለታ አስተዳደር የስራ ሂደት ተወካይ ይገልጻሉ፡፡

ተወካዩ አቶ አቡበከር አህመድ እንደሚሉት ግንባታው በ2009 ዓ.ም መጨረሻ ላይ አፍሮጽዮን ኮንስትራክሽን ከተባለ ኩባንያ ጋር በተደረገው ስምምነት በ800 ሚሊየን ብር የውል ስምምነት የተጀመረ ሲሆን በ2010 ለሚከበረው የብሄር ብሄረሰቦች በአል እንዲደርስ በሚል በፍጥነት ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በውሉ መሰረት ግንባታው በ2012 ዓ.ም ተጠናቆ ርክክብ መፈጸም የነበረበት ቢሆንም በዓሉ ካለፈ በኋላ ድርጅቱ ግንባታ ለማካሄድ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠረ ማዘግየቱን የሚናገሩት አቶ አቡበከር፤ ግንባታው እንዲጠናቀቅ ክልሉ ተመላሽ የሚሆን ተጨማሪ ገንዘብ ለተቋራጩ ሰጥቶ እንደነበርም ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም ስራው ምንም ፈቅ ሳይል ተቋርቷል ይላሉ፡፡

በአንጻሩ ተቋራጩ ከአጠቃላይ ክፍያው ውስጥ 81 ከመቶውን መውሰዱን የሚናገሩት አቶ አቡበከር፤ አሁን ካለው የዋጋ ንረት አንጻር በቀረው በጀት ግንባታውን ማጠናቀቅ ከባድ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ አቡበከር ገለጻ፤ ይህ ስራ ለተቋራጩ የተሰጠበትም መንገድ ቢሆን በጨረታ አልነበረም፡፡ ኮንትራክተሩ በወቅቱ በካቢኔ ውሳኔ ከዚህ በፊት ሌሎች ስታዲየሞችን ሲሰራ ነበር በሚል ያለጨረታ ነው የተሰጠው፡፡

አፍሮጽዮን ኮንስትራክሽን ደግሞ ሲሳይ ደስታ የተባሉ የሽብር ቡድኑ ሕወሓት አባል የነበሩ ግለሰብ ባለቤትነት የተዘመገበ ድርጅት ሲሆን የድርጅቱ ባለቤትም ለውጡን ተከትሎ ሃገር ጥለው በመውጣታቸውና ድርጅቱም በመዘጋቱ ስራው ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል ይላሉ አቶ አቡበከር፡፡

በዚህ የተነሳም በአሁኑ ወቅት ስታዲየሙ ርክክብ ሳይደረግበት ባለበት በመቆሙ ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦበታል፡፡

የግንባታው ተቆጣጣሪ ኤምኤች ኢንጂነሪንግ የተባለ ኩባንያ ሲሆን የኩባንያው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ አቶ የማነ መልካሙ ግንባታው ባለፉት አስር ወራት ሙሉ ለሙሉ መቆሙን ይገልጻሉ፡፡ በዚህ የተነሳም ለሰራተኞች ደመወዝ አልተከፈለም፡፡ ከዚህም ባሻገር የተቋራጩ ባለቤት ሃገር ውስጥ ባለመኖራቸውና ቢሮአቸውም በመዘጋቱ ማንንም ማነጋገር አልተቻለም፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው አማራጭ በህጋዊ መንገድ ክስ መስርቶ መጠየቅ ብቻ ነው፡፡

"ኮንትራክተሩ ስራውን አደጋ ላይ ጥሎ ነው የሄደው" የሚሉት አቶ የማነ፤ ከዚህ በኋላ ግንባታው እንዳይበላሽ ቶሎ ወደውሳኔ መግባት እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

የአፋር ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር መሐመድ ሁመድ በበኩላቸው ይህ ችግር በሃገር አቀፍ ደረጃ ጭምር የተፈጠረ ነው፡፡ ከዓመታት በፊት በመላ ሃገሪቱ የተጀመሩት ስታዲየሞች ግንባታ የጥቂት ቡድኖችን ኪስ ለማደለብ ካልሆነ በስተቀር በጥናት ላይ ተመስርተውና አዋጭነታቸው ተገምግሞ አልነበረም፡፡ የሠመራ ስታዲየምም ለአፋር ሕዝብ ታስቦ የተጀመረ አይደለም፡፡

በአሁኑ ወቅትም ይህ በርካታ የሃገር ሃብት የፈሰሰበት ስታዲየም በዚህ መልኩ ቆሞ መቅረት ስለሌለበት ቢሮው አጠቃላይ ስታዲየሙ ያለበትን ቁመናና በቀጣይ መስተካከል ያለበትን ደረጃ በማስጠናት ወደስራ ለማስገባት እየሰራ ነው የሚሉት ኢንጂነር መሃመድ፤ ከዚህም ባሻገር ጉዳዩን በሕግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ እንደሆኑም ተናግረዋል።

የኤፌዴሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው በሃገራችን በግንባታ ላይ ላሉት 16 ስታዲየሞች ግንባታ እና እድሳት በጠቅላላው 18 ቢሊዮን 450 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎባቸዋል፡፡

ሆኖም የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን/ካፍ/ ባወጣው መስፈርት መሰረት እነዚህ ስታዲየሞች ዓለምአቀፋዊም ሆነ አህጉራዊ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ ብቁ አይደሉም፡፡ በዚህ የተነሳ መስፈርቶቹን ለማሟላት የሚያስችሉ ተጨማሪ ስራዎች ያስፈልጋሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት ስታድየሞችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ለማጠናቀቅ በሀገራዊው የስፖርት ፋሲሊቲ ፎረም ላይ አቅጣጫ ተቀምጦ በልዩ ሁኔታ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ የሚያትተው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር መረጃ የፌዴራል መንግሥትም በልዩ ሁኔታ ክትትልና ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

በዚህ መልኩ ለባከነው የሀገርና የሕዝብ ሃብት ፍትሃዊ ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ ጀምሮ ፕሮጀክቱን ወደ ሥራ ለማስገባት የክልሉ መንግሥት፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና የሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

# ‹‹የግድቡን ቀሪ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማስቀጠል እንደሚገባ አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የግድቡን 11ኛ ዓመት አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ በቀጣይ ቀሪ የግንባታ ተግባራትን በውጤታማነት ለመፈጸም የሰፊውን ማህበረሰብ ተሳትፎ እና ድጋፍ በተሻለ መንገድ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የመሰረት ድንጋይ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ ግድቡ ወሳኝ የግንባታ ሂደቶችን በማለፍ በአሁኑ ጊዜ ሃይል ማመንጨት ጀምሯል ሲሉ አስታውሰዋል፡፡

በዚህ ታሪካዊ የግንባታ ጉዞ የሕዝባችን ሁለገብ ድጋፍ፤ የመንግሥት ጠንካራ አመራር፤ የዲያስፖራ ወገኖቻችን እገዛ እንዲሁም የፕሮጀክቱ አመራሮች እና ባለሙያዎች ርብርብ በእጅጉ የሚደነቅ እና የሚያኮራ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ቀሪ የግንባታ ተግባራትን በውጤታማነት ለመፈጸም የሰፊውን ማህበረሰብ ተሳትፎ እና ድጋፍ በተሻለ መንገድ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ለሺ ዓመታት ሲፈስ የነበረው የዐባይ ወንዝ ለሃገራችን ሁነኛ የልማት አቅም ለመሆን በሩ የተከፈተበትን ታሪካዊ ዕለት በጋራ ለመዘከር አበቃን ብለዋል።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት በተለያየ መልክ የሚገለጹ ችግሮች ሃገራችንን እየፈተኗት ቢሆንም፤ በታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሂደት ላይ የተስተዋለውን የጸና ህዝባዊ አንድነት እና ህብረት የበለጠ አጠናክሮ በድል ማሻገር ይጠይቃል ብለዋል።

ከቀደሙ አባቶቻችን የወረስነውን የድል አድራጊነት ጠንካራ መንፈስ ለመጪው ትውልድ የታፈረች፣ የተከበረች እና የበለፀገች ሃገር ለማስረከብ አንድነታችንን እና ህብረታችንን አጥብቀን ልንጓዝ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፣ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፣ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በዐቢይ አራት ሻማዎች ጭላንጭል... ! ?

በዚች ሀገር የ"100"፣ የሦሥት ሺህም ሆነ የሰባት ሺህ ዓመት ዘመናዊ ሆነ ጥንታዊ የአገረ መንግሥት ታሪክ እንደ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መንግሥት እና እንደዚህ ሕዝብ በኃይለኛ የውቅያኖስ ማዕበል (ሱናሚ ) መካከል እንደምትቀዝፍ ታንኳ ከየአቅጣጫው የተላጋ ፣ የተናወጠ ፣ የተፈተነና መልሕቁን ለመጣል የተቸገረ የለም ማለት እችላለሁ ። ታሪካዊ ንጽጽሬ ላይ የዘመነ ጓዴነት /contemporaries/ ጥያቄ የሚያነሳ ካለ ደግሞ እንዲህ ላስተካክለው፡- ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ በየትኛው አህጉር ያለ አገርና ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ የተፈተነ የለም። የመንም ፣ ሊቢያም ፣ ሶሪያምና ሶማሊያም ፣ ሌላም አገር ቢሆን ።

ለውጡ የባተበትን አራተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ይሄን ዘካሪ መጣጥፍ አራት ሻማዎችን ለኩሼ እያጠናቀርሁ እያለ እንኳ ፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በምስራቅ ሸዋ ፈንታሌ ወረዳ ቆርኬ አካባቢ በአካባቢ ሚሊሻና በፌደራል ፓሊስ አባላት ላይ አክራሪ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት ለተገደሉ የሐዘን መግለጫ ያወጣ ሲሆን፤ ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን አድኖ ለሕግ ለማቅረብ የሚያደርገውን ጥረት ሕዝብ እንዲተባበረው ጠይቋል። እንዲሁም የአማራ ክልል ፤ የአማራን ሕዝብ እረፍት ለመንሳትና ከአጎራባች ክልሎች ጋር ለማጋጨት አክራሪ ኃይሎች በቅንጅት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን በመግለጽ ሕዝብ ከጎኑ እንዲሰለፍ ጥሪ አድርጓል ።

በአማራና በአፋር ክልሎች በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ የተነሳ ከ12 ሚሊየን በላይ ወገኖች ፤ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ የአርብቶ አደሩ የህልውና ዋስትና የሆኑ እንስሳት አልቀው በሚሊዮኖች የሚገመት ሕዝብ የዕለት ደራሽ እርዳታ ፈላጊ ሆነዋል። በአናቱ የቀደሙትንና ሰሞነኞዎችን ሳይጨምር እስከ አለፈው አመት በአገሪቱ 113 ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ጭፍጨፋዎች ፣ ጥቃቶችና ግጭቶች በተቀናጀ አግባብ መፈጸማቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ መናገራቸውን ያስታውሷል ።

በመላ አገሪቱ እየተስተዋለ ያለው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ሕዝቡን ክፉኛ እያማረረ ባለበት በዚህ ፈታኝ ሰዓት ፤ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ፤ የአሜሪካ ጥቂት የኮንግረስ አባላት ኤች አር 6600 እንዲሁም ኤስ 3199 የተሰኙ ረቂቅ ሕጎችን በማዘጋጀት እጅ አዙር የጭቆና ቀንበራቸውን ለመጫን እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ፤ ዶ/ር ቴዎድሮስ ፣ አቡነ ማቲያስና በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ያለው የሕወሓት ጭፍራ ይህ የማዕቀብ ሕግ እንዲጸድቅ በተናበበ መንገድ ጥረት እያደረገ ይገኛል ። (እዚህ ላይ ሕወሓት አቡነ ማቲያስን እንደፈለገ ቁጭ ብድግ የሚያደርጋቸው ፤ ከሲኖዶሱም ሆነ ከቤተክርስቲያኗ ቀኖና ውጭ ለዛውም በዓቢይ ጾም እንዲህ ያለ መግለጫ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው አንዳች ማስፈራሪያ ወይም (blackmail) ማድረጊያ ነገር ሳይዝባቸው አይቀርምና የሚመለከተው አካል ምርመራ ማድረግ ይገባዋል፤ የሚል ሀሳብ አለኝ) ።

ይሁንና ሁሉም ነገር ተስፋ አስቆራጭና ድቅድቅ ጨለማ ነው ማለት አይደለም ። ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ከክሽፈት ተርፎ በአንድ ተርባይን 375 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት መቻሉ በራሱ ትልቅ ስኬት ቢሆንም የቀጣናውን ጂኦፖለቲካ በመበወዝ የሚኖረው ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነው ። በድህነታችንና በተመጽዋዕችነታችን ሳቢያ ፖለቲካዊ ብቻ የነበረውን ግማሽ የነጻነትና የሉዓላዊነት ታሪካችን ሙሉ የሚያደርግ የበጋ ስንዴ ልማት ሌላው ተስፋ የሚያሰንቅ ተግባር ነው ። 430ሺህ ሔክታር የበጋ ስንዴ ማምረት ባንችል ኖሮ በራሽያና በዩክሬን ጦርነት የተነሳ ጣራ የነካውን የስንዴ ዋጋ በምን ጎናችን እንችለው ነበር ። የቀድሞው የኢሳት ጋዜጠኛ ደረጀ ሀብተወልድ ይሄን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ውሳኔ ዘመኑን አበክሮ የዋጀና ትንቢታዊ ነው ይለዋል ። የዩክሬንና የራሽያ ጦርነት እንደሚቀሰቀስ ቀድመው ያወቁ ይመስል የበጋ ስንዴ በማስጀመራቸው ነው ውሳኔያቸውን ትንቢታዊ ነው ያለው ። ኩታ ገጠም ግብርና እና ሜካናይዜሽን ላይ እየተሠራ ያለው ሥራም ተስፋን የሚያለመልም ነው ። የአረንጓዴ አሻራውና የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቱም የብሩህ ተስፋችን ቡቃያ ነው ።

አገራዊ ምክክር ለማድረግ መንግሥት ኮሚሽን በአዋጅ ማቋቋሙና ኮሚሽኖች በገለልተኛ አካል እንዲሰየሙ መደረጉ ፤ አካታች አገራዊ ምክክሩ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል ነው ። በማንነት በልዩነትና በጥላቻ የተጎነቆለውን ፖለቲካችንን እልባት የሚሰጥ ነው ። አገረ መንግሥቱን ከተቀለሰበት ድቡሽት አንስቶ በጽኑ መሠረት ላይ የሚያንጽ ነው። ትውልዶች ለዘመናት ሲያነሷቸው ሲታገሉላቸውና መስዋዕት ሲከፍሉላቸው የኖሩ ጥያቄዎችን በማያዳግም ሁኔታ የሚመልስ ነው ። አገራዊ ምክክሩ የጋራ አገር ፣ የጋራ ሕልም ፣ የጋራ ራዕይ ፣ የጋራ ሰንደቅ አላማ ፣ የጋራ ጀግና ፣ የጋራ ታሪክ ፣ ወዘተረፈ. እንዲኖረን የሚያግዝ ነው ። ገለልተኛነቱ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ከተመለሱና በቅንና ንጹሕ ሕሊና ከተመራ የትውልድ ተስፋና ለአገርም ወሳኝ መታጠፊያ/critical juncture/ ነው ። አገርን እንደ ንስር የሚያድስና በከፍታ የሚያበር ነው ።

የብሔራዊ ምክክሩን አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለፈው ዓርብ በማኅበራዊ ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት ፤ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ታሪክ የሚቀይሩ ወርቃማ የለውጥ ዕድሎች ገጥመዋታል ። ፖለቲካችንን አንድ ደረጃ ወደፊት የሚያስፈነጥሩና ቀጣይ ዘመናችንን ብሩህ የሚያደርጉ እያሌ የለውጥ ችቦዎች ተለኩሰዋል። እነዚያ ለውጦች የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር አለ፤ ቁጭት ። በቁጭት ተጠንስሰው ፣ በቁጭት ተካሂደው፣ በቁጭት ይጠናቀቃሉ ። አብዛኛውን ጊዜ የለውጥ ምዕራፎች በሚጀምሩበት ወቅት የምንሰንቃቸው የለውጥ ሐሳቦች ዳር ከመድረሳቸው በፊት ሲኮሰምኑ በተደጋጋሚ አይተናል ። በለውጥ በሂደት ወቅት ግባችንን ለማሳካት ከመተባበር ይልቅ በጥቃቅን ጉዳዮች እርስ በእርስ መጓተቱን ስለምናስቀድም በመጀመሪያ ያስጎመጅ የነበረው የለውጥ ፍሬ በመንገዱ መሐል ተጨናግፎ ይቀራሉ ።

መጨናገፋቸውን ልብ የምንለው ዘግይተን በመሆኑ ዕድሎቹ ካለፉ በኋላ እንደ አገር መልሰን እንቆጭባቸዋለን። እኛ የቀደመውን ትውልድ "ይሄንና ያንን ቢያደርግ ኖሮ" እያልን እንደምንወቅሰው ሁሉ፣ የቀደመው ትውልድም ከእሱ በፊት የነበረውን ትውልድ ሲኮንን ነበር። ከዚህ የታሪክ አዙሪት ለመውጣት እስካልወሰንን ድረስ ነገ የእኛም ዕጣ ካለፈው የተለየ አይሆንም ። ዛሬ በቸልታ የምናልፋቸው አጋጣሚዎች ተደምረው ነገ ላይ የልጅ ልጆቻችን እኛን የሚወቅሱበት ምክንያት ይሆናል ። ይህ እንዳይሆን ዛሬ እጃችን ላይ የሚገኙ የለውጥ ዕድሎችን ሁሉ አሟጥጠን ለመጠቀም መረባረብ አለብን ። ለዘመናት እየተንከባለሉ ዛሬ ላይ የደረሱ የፖለቲካ ፈተናዎቻችንን በጉልህ መቅረፍ የሚያስችለንና መጻዒ ዘመናችንን አዲስ መሠረት ላይ የማቆም አቅም ያለው ብሔራዊ የምክክር ሂደት ዛሬ በእጃችን ላይ ያለ ወርቃማ ዕድል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ይህን ወርቅ የሆነ አጋጣሚ የስንት ልፋት እና የስንት ታሪክ ሂደት ውጤት መሆኑን ዘንግተን እንደ ጠጠር ከቆጠርነው በቀላሉ ልናጣው እንችላለን ። በተቃራኒው እንደ ዕንቁ አክብረንና ተንከባክበን ከተጠቀምንበት ዋጋው ከፍ ያለና ታሪክ ቀያሪ ዕድል ይሆናል ። ልጆቻችንም "አባቶቻችን እንዲህ በማድረጋቸው አገራችን እዚህ ከፍታ ላይ ደረሰች" ብለው የሚያመሰግኑበትን አጋጣሚ ይፈጥራል ።

አካታች ብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ሒደቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መከናወን አለበት ። ይኸም የሚሆነው ሁላችንም የምክክር ሂደቱን በበላይነት የሚመራውን የምክክር ኮሚሽን በተለያዩ መንገዶች መደገፍ፣ ማትጋትና ማጽናት ስንችል ነው ። በዚህ ጉዳይ ዳር ቆሞ መገኘት በታሪክ ፊት የሚያስወቅስ ተግባር ነው። ሁሉም አካል በባለቤትነት ስሜት ለምክክር ሂደቱ አስተዋጽዖ በማድረግ ተሳትፎውን ያረጋግጣል እንጂ አንዱ ጋባዥ ሌላው ተጋባዥ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ከታሪክ ተጠያቂነት ነጻ አያደርግም ።

በመንግሥት በኩል እስከ ታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ድረስ የተቋቋመው የምክክር ኮሚሽን በቅልጥፍና መሥራት እንዲችል አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም ። የክልል መስተዳድሮች ቀናነት፣ ባለቤትነትና ታሪካዊ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ግብአት በማቅረብ ለሥራው ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል ። ተፎካካሪ ፓርቲዎች በውይይቱ እንደሚሳተፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ሂደቱ ባለቤት ለሂደቱ ቅልጥፍናና ስኬት አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ በትኅትና እጠይቃለሁ ። ምሁራን ኮሚሽኑ አስተያየትና ምክረ ሐሳባችሁን በሚፈልግበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ ተነሣሽነት ፤ የሂደቱ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የታሪካዊ ጉዟችን እና የዘመን አሻራችን ለሆነው ምክክር አስተዋጽዖዋችሁ የላቀ እንዲሆን እማጸናለሁ ።

የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች አገር ስምምነትን በምትፈልግበት በዚህ ወቅት አማካይ ሆናችሁ ሁሉን የማስማማት አደራ አለባችሁና የመቀራረቢያውን መድረክ በማገዝ አገራዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ ከልብ በመነጨ ትኅትና እጠይቃለሁ ። የሁሉም ኃላፊትነት ተደምሮ የሚወድቀው በአገርና በሕዝብ ትከሻ ላይ ነው ። ሁላችንም ልዩነቶቻችንን አቻችለን በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ አለብን ። ሕዝብ ያላከበረው እና ሕዝብ ያልደገፈው እንቅስቃሴ ውጤቱ መና ነውና መላ ኢትዮጵያውያን ድጋፋችሁ ፣ ተሳትፏችሁ ፣ ክብራችሁና ጸሎታችሁ ከኮሚሽኑ እንዳይለይ ከታላቅ አክብሮት ጋር እጠይቃለሁ ሲሉ ዶ/ር ዐቢይ ጥሪ አድርገዋል ።


በዚህ መጣጥፍ መግቢያ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አገራችን በታሪኳ ባለፉት ሰባት ዓመታት በተለይ ለውጡ ከባተ ወዲህ ባሉት አራት ዓመታት የገጠማትን አይነት ፈተና በታሪኳ ገጥሟት አያውቅም። ለዚህ ነው እነዚህን ፈታኝ የለውጥ ዓመታት በንፋስ ሊጠፉ በተቃረቡና በሚስለመለሙ አራት ሻማዎች ወክዬ የዐቢይ አራት ሻማዎች ጭላንጭል ያልኳቸው ። ኮንፊሽየስ ፣ " ሺህ ጊዜ ጨለማን ከመውቀስ አንድ ሻማ መለኮስ ይሻላል ።" እንዳለው፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩና የለውጥ ኃይሉ በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ከአንድም ሁለት ሶስት አራት ሻማዎችን በመለኮስ የኮንፊሺየስን ምክረ ሀሳብ የሰሙ ይመስላል ። ያው ሻማዎቹን የዐቢይ ብላቸውም በውስጠ ታዋቂነት መላው የለውጥ ኃይል ፣ እኔ ፣ አንተ ፣ አንቺ አለን ። ሆኖም ከንፋሱ ጋር እየታገሉ በሚሰጡት የብርሃን ፀዳል ጨለማውን አሸንፈው ወገግ ማለታቸው ፤ በቁጥርም መበርከታቸው አይቀርም ። ጨለማውን ከመርገም የተለኮሱ ሻማዎች እንዳይጠፉ የዜግነት ግዴታችንን እንወጣ !!! አሜን።

> **አገራችን በታሪኳ ባለፉት ሰባት ዓመታት በተለይ ለውጡ ከባተ ወዲህ ባሉት አራት ዓመታት የገጠማትን አይነት ፈተና በታሪኳ ገጥሟት አያውቅም። ለዚህ ነው እነዚህን ፈታኝ የለውጥ ዓመታት በንፋስ ሊጠፉ በተቃረቡና በሚስለመለሙ አራት ሻማዎች ወክዬ የዐቢይ አራት ሻማዎች ጭላንጭል ያልኳቸው ። ኮንፊሽየስ ፣— ሺህ ጊዜ ጨለማን ከመውቀስ አንድ ሻማ መለኮስ ይሻላል ።" እንዳለው፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩና የለውጥ ኃይሉ በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ከአንድም ሁለት ሶስት አራት ሻማዎችን በመለኮስ የኮንፊሺየስን ምክረ ሀሳብ የሰሙ ይመስላል**

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹ወታደርነት አርቆ አስተዋይነትን የምንላበስበት ማሕጸን ነው››

- ባሻ ዳምጠው ገብረሕይወት
የቀድሞ ሰራዊት ባልደረባ



**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የሕይወትን ቅመም የምንፈልግበት መንገድ ብዙዎቻችንን ወደተለያየ የሙያ መስክ ያስገባን ይሆናል። ነገር ግን ያለፍላጎታችንም ሙያዎችን መርጠን ልንገባ የምንችልበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ ደስታችን ውስንነት እንደሚኖርበት እሙን ነው። ሕይወት መስመራችንን ስትጠቁመን ሠርተን መኖር ስላለብን ብቻ የምንመርጣቸው መስኮች ይኖራሉ። እናም በዚያ ውስጥ ሆነን ዓመታት ያልፋሉ። ጊዜያትም ይነጉዳሉ። የፈለግነው ላይ የማንደርሰውም ከዚህ የተነሳ ይመስላል።

የሙያ ምርጫችን ልጅነታችን ላይ የፈለግነው ከሆነ ደግሞ ዘላለም ደስተኛ እንሆናለን። ምክንያቱም ስኬታችንን እንደፈለገን ልንመራውና ልናገኘው እንችላለን። ለአዳዲስ ፈጠራና ሁነቶች ተቀባይነታችንም የሰፋ ይሆናል። ምክንያቱም ህልማችንን ለማሳካት የማንቆፍረው ድንጋይ የለምና። የዛሬው የሕይወት እንግዳችን ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው። ከልጅነታቸው ጀምሮ ውትድርና ሙያቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ። ሕልማቸውም አባታቸውን መተካት ነበር፤እንዳሰቡትም ፈጽመውታል። ከዚያም አልፈው ልጆቻቸውን ተከታይ አድርገዋቸዋል።

እንግዳችን ባሻ ዳምጠው ገብረሕይወት ይባላሉ። በውትድርና ሙያ ረጅሙን የሕይወት ክፍል አሳልፈዋል። እንደውም ወጣትነታቸውን በሚገባ የሠሩበት ቦታ እርሱ እንደሆነ ይናገራሉ። ለማንም አልታዘዝ ያለው ማንነታቸው በዚያ ተቀጥቷል፤ ሥርዓትንም ተምሯል። እናም ይህንን ቦታ ‹‹ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን የዛሬ መኖሬ ምክንያት ነው›› ይሉታል። ከዚህ ልምዳቸው በመነሳትም ሰዎች በተለይ ወጣቶች ራሳቸውን ለማየትና አገራቸውን ለመውደድ ይጠቀሙበታል የሚሉትን ብዙ ሀሳቦች በሕይወታቸው አካተው ነግረውናልና ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ።

### የአባቱ ልጅ

ባሻ ዳምጠው ተወልደው ያደጉት በቀድሞ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት መቀሌ ከተማ ሲሆን፤ በ1935 ዓ.ም ይህችን ምድር ተቀላቅለዋል። ለዚህ ደግሞ አባታቸው ማይጨው ዘማች መሆናቸው በቦታው ላይ እንዲወለዱና እንዲያድጉ አድርጓቸዋል። በዚህም ከትግራይ የወጡት የስምንት ዓመት ልጅ ሳሉ ነው። በእርግጥ ይህም ቢሆን በአንድ አጋጣሚ የሆነ ነው። አባታቸው ከተወለዱበት አካባቢ ከአንድም ሰባት ቤተሰብ ሞቶ በመረዳታቸው ወደ ትውልድ ቀያቸው አቀኑ። ነገር ግን መመለስ አልቻሉም ነበር። ትንሹ ዳምጠውም አብረዋቸው ስለነበሩ በዚያው ቀሩ። እናታቸው ግን አካባቢያቸውን ለቀው መሄድ አልፈለጉምና ልጅና እናት ተለያይተው እንዲኖሩ ሆነዋል። በእንጀራ እናትም የማደጋቸው ምስጢር ይህ ነው።

እናታቸውን በጣም የሚወዱት ባለታሪካችን፤ እስከ ስምንት ዓመታቸው የነበረው የልጅነት ጊዜያቸው እጅግ ጣፋጭ ነበር። ደስታቸውን ያጣጣሙበትና ተምቤን ድረስ በመሄድ ብዙ ትዝታ ያፈሩበት እንደነበር አይረሱትም። በተለይም በአያቶቻቸውና በእናታቸው ቤተሰቦች የሚደረግላቸው ነገር ዘላለም ከአዕምሯቸው የማይጠፋ ነው። ሁሌም ቢደገምልኝ የሚሉት አይነትም ነው። ነገር ግን አልሆነም። ምክንያቱም እናታቸው ከአጠገባቸው የሉም። የሚተዳደሩትም ሆነ የሚኖሩት በእንጀራ እናት ነው። አባታቸው በጣም ይንከባከቧቸዋል። ነገር ግን በቤት ውስጥ ብዙም ስለማይውሉ እንጀራ እናታቸው ብዙ ስቃይን ታበዛባቸው ነበር። በዚህም በመማረራቸው የተነሳ አንድ ቀን እግሯን እንደሰበሩት አይረሱትም።

ለእናታቸው የመጀመሪያ ልጅ በመሆናቸው ደስተኛ መሆንን እንጂ ስቃይን አያውቁም። በዚህም የእንጀራ እናታቸው በምታደርገው ነገር በትንሹም በትልቁም ይማረሩም ነበር። በዚህም ኃይለኛና ተደባዳቢ ልጅ ሆኑ። ትንሽ ከነኳቸው ልጆችን ሁሉ ይደባደባሉ። እንደውም መምህር ጭምር የደበደቡበት ጊዜም እንደነበር ያስታውሳሉ። ይህ ደግሞ ማረሚያ ቤት እንዲመላለሱ አድርጓቸዋል። በተደባዳቢነታቸውም ማረሚያ በየጊዜው የሚገቡበት ቤታቸው ነበር። በዚህም የግንደበረት ቆይታቸው ብዙ ነገር የተደበላለቀበት እንደነበር ያነሳሉ።

ፈረስ ጉግስና የገና ጨዋታ በጣም ይወዳሉ። ለጨዋታ በወጡበት ሰው ሳይፈነክቱ አይገቡም። ይህ ደግሞ ለእስር ይዳርጋቸዋል። ግን ወደውት የሚያደርጉት ስለሆነ ምንም አይመስላቸውም። ይሁን እንጂ ለአባታቸው እዳ ሆነውባቸው ነበር። ምክንያቱም በየጊዜው ዋስ እየሆኑና ለተበዳዮች ካሳ መክፈሉ ያማርራል። ልጃቸው ስለሆኑ ብቻ ነው የሚያደርጉት። አንድ ቀን ግን ይህም ቢሆን መሯቸዋል። ቤቴ እንዳይመጣ ያሉበት ጭምር ነበር። ጉዳዩ መምህራቸውን የደበደቡበት አጋጣሚ ሲሆን፤ ትምህርቱንም እንደማይቀጥሉበት ያውቃሉና የደረሰበት ይድረስ አሏቸው። እርሳቸውም ቢሆን ችግር ፈጣሪነታቸውን ተረድተውታልና ወደ ቤትም ሆነ ወደ ትምህርት ቤት ሊገቡ አልፈለጉም። በዚህም ቦታውን ለቀው ወጡ።

ማረሚያ ቤት በተለይም ለወንድ ልጅ ብዙ ነገር የሚያቃልልና የሚያራግፍ ነው። በንብረት፣ በሕይወትና መሰል ነገር የመጣን ሁሉ ያስቆማል የሚሉት ባለታሪካችን፤ በዚያ በቆዩባቸው ጊዜያት ትልቅ ትምህርት እንዳገኙና የዛሬውን መስመራቸውን እንዲይዙ እንዳደረጋቸውም ያወሳሉ። ከአባታቸው የወረሱት የወታደርነት ሙያም እውን የሆነው በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። በእርግጥ ሙያውን ይወዱታል፤ የልጅነት ሕልማቸውም ነው። ግን በደንብ ያወቁትና የተረዱት በማረሚያ ቤት ያገኙት ልምድ ሲታከልበት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እህታቸው ጋር በአምቦ ከተማ ለትንሽ ጊዜ ቆይተውም ነበር። ይህ ደግሞ ሌላ እድል የሰጣቸው ነው። የመወደድና ደስተኛ የመሆን። ነገር ግን እንደወታደር ቤቱ ምንም እንደማይሆንላቸው ያስታውሳሉ። ምክንያቱም ይህ ቤት የእናት ቅጣት፣ የእናት እንክብካቤና ፍቅር ያለበት ነው። በዚያ ደግሞ ዘላለም መኖር ደስታን እንጂ ኃዘንን አያመጣም። እናም በዚያ የቆዩበት ጊዜ ከስምንት ዓመት በፊት ከእናታቸው ጋር ያሳለፉትን ጊዜ እንደሚያስታውሳቸውም ይናገራሉ።

ባሻ ዳምጠው፤ አባታቸውን ሲያገለግሉ ለጉልበታቸው ሰስተው አያውቁም። ከትምህርት ውጪ ባለው ጊዜያቸው በረሃ ወርደው እንጨት ይሰብራሉ፤ ውሃ ከርቀት ተመላልሰው ይቀዳሉ፤ ቤት በሳር ስለሚሠራ ሳሩን ከማጨድ እስከ መከመርና ቤቱን መሥራት ድረስ የእርሳቸው ኃላፊነት እንደሆነ አስበውም የሚተጉ ናቸው። እንደውም ‹‹እንደእኔ ይህንን ያህል የሚሠራ የለም›› ይላሉ። ምክንያቱም በቀን ውስጥ ጊዜ ካላቸው እስከ አራት ሸክም ያህል ይከምራሉ። በዚያ ላይ ለከብት የሚሆንም ሳርም በብዛት ያመጣሉ። ነገር ግን ይህ ሁሉ አገልግሎታቸው በአባታቸው ትልቅ ቦታ ቢኖረውም በእንጀራ እናታቸው እንደእገዛ አይታይም። የአባታቸውም ቢሆን በነበራቸው ኃይለኝነት ምክንያት ትኩረት ተነፈገው። ስለዚህም በዚያ ቤት የነበራቸው ትዝታ የውሃ ሽታ እንደሆነ ያስባሉ።

### ስምንትን ያልዘለለው ትምህርት

ከትምህርት ጋር የተዋወቁት በቄስ ትምህርት ነው። ትምህርቱ በግዴታ የሚሄዱበትና ውለው የሚገቡበትም ቢሆን ብዙ ነገርን አስተምሯቸዋል። የጉብዝናቸው ምንጭም ሆኖላቸዋል። በተለይም አንደኛ ክፍል ሲገቡ ከሁሉም ተማሪ የተሻለ አቅም ነበራቸው። ከዚያም በኋላ ቢሆን የደረጃ ተማሪነታቸውን ማንም አልነጠቃቸውም። በራሳቸው ባህሪ ችግር እንዳልሆነ አደረጉት እንጂ። ይህም ትምህርታቸውን ሲያቋርጡ የሆነው ነው።

በግንደበረት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን የጀመሩት ባሻ ዳምጠው፤ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን የተከታተሉት ከዚሁ ትምህርት ቤት ሳይወጡ ነው። ከዚያ በኋላ ያለው ጊዜያቸው ያለፈው በውትድርናው ሙያ ውስጥ ነበር። ሁሉም ሰው መደበኛውን ትምህርት ካልተከታተለ አልተማረም እንደማይባል ሁሉ እርሳቸውም መደበኛውን ወደ ትምህርት መስክ ቀይረውት እንዲማሩ ሆነዋል።በውትድርናውም ውስጥ በርካታ የስልጠና አይነቶችን በመውሰድና በመመረቅ አገራቸውን አገልግለውበታል።

ከስምንተኛ ክፍል በኋላ ላለመቀጠላቸው ምክንያቱም አሁንም አትንኩኝ ባይነታቸው ሲሆን፤ ዱላ ወዳድነታቸው ትምህርቱን እንዲያቋርጡት አድርጓቸዋል። መነሻው ደግሞ ከርዕሰ መምህሩ ጋር በጋራ በወደዷት ልጅ መጋጨታቸው ነው። ዘልፈዋቸው በብዙ ሰዎች ፊት አዋረዷቸው፤ ተደባደቡም። በዚህም ለእስር ተዳረጉ። ከእስር ሲፈቱ አባታቸውም አንቅረው እንደተፏቸው ተረዱ። ከማኅበረሰቡም ጋር ቢሆን በዚያ ሁኔታ እንደማይቀጥሉ አወቁ። በዚህም ትምህርታቸውንና ያደጉበትን ቀየ ትተው ወደ አዲስ አበባ ተሰደዱ።

አዲስ አበባ አክስታቸው ልጅ ጋር አረፉና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወጣ ብለው ጓደኞቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ወታደር ካምፕ አመሩ። ጊዜው ደግሞ ውትድርና የሚመለመልበት ነበር። በዚህም ጓደኛ ለመፈለግ የሄዱት ባለታሪካችን፤ የልጅነት ህልማቸውን አገኙት። አቋምና ቁመናቸው ለውትድርናው የተመቸ በመሆኑም በቀጥታ ነበር የተመለመሉት። ሆኖም ፈተና ነበረው። ይህም ቢሆን ለእርሳቸው ቀላል ነበረና ከተመረጡ ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ ሆኑ።

ውትድርናው ውስጥ ከገቡ በኋላ የተለያዩ ስልጠናዎችን የወሰዱ ሲሆን፤ የመጀመሪያው መሠረታዊ የውትድርና ትምህርት ነው። ከዚያ ተምሮ ማስተማር ስልጠና አዋሽ አርባ ገቡ። በነበልባል ክፍለ ጦር ውስጥም በመሆን በማመላለሻ ትምህርት ቤት በልዩ ልዩ ሕጎችና ፖሊሳዊ ትምህርት ሰለጠኑ። ቀጥለውም የመሣሪያ ትምህርትና ልዩ ልዩ የጸረ ውንብድና ስልቶችን በመማር ተመረቁ። የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስም ስልጠናንም እንዲሁ ወስደው ተመርቀዋል። የአሽከርካሪነት ትምህርትም ተምረዋል።

### ሥራና ጅማሮው

መጀመሪያ ከሥራ ጋር የተገናኙት በወሰዱት ትምህርት ለማሰልጠን ደብረ ዘይት ለምለም ጣቢያ ውስጥ ነው። አጭር ወር የቆዩበትም ቢሆንም ብዙዎችን አፍርተውበታል። ከስምንት ወር በኋላ ደግሞ የአገሪቱ ሁኔታ የተረጋጋ ስላልነበር ወደ ዘመቻ ገቡ። ይህም የሶማሊያ ሰርጎ ገብ ገባ በሚባልበት ጊዜ መሆኑ ነው። እናም ጓድ መሪ ወይም አዋጊ ነበሩና ወራሪውን ለመመከት በባቡር ተጭነው ጦሩን ተቀላቅለው ተጓዙ። ከባቡሩ ከወረዱ በኋላም መንገዱን እያጠሩ ሁርሶን ይዘው እስከ ድሬዳዋ ዘለቁ።

አሁንም በአይሻ ደዎሌ በኩል ሰርጎ ገቦች ታይቷል ሲባሉ ሥራቸው አገርን ከወራሪ መታደግ ነውና ጓዛቸውን ጠቅልለው ተነሱ። የእለት ሥራቸውን መከወንም ጀመሩ። እስከ አዲጋላም በመሄድ ነጻ የማውጣቱን ተግባር ፈጽመዋል። ወደ ሐረርም በመዞር ይህንኑ ተግባራቸውን ሲከውኑ ቆይተዋል። አሁንም ‹‹ጎዴ ዋቢ ሸበሌ ተያዘ፤ ጦሩ የሚጠጣው ወሃ የለውም›› ሲባሉ ወደዚያው በማምራትና በርካታ ትግሎችን በማድረግ የወገንን ኃይል ለድል አብቅተዋል። ይሁን እንጂ መልሶ ማጥቃት ሲጀመር ግን ለእርሳቸው ጥሩ እድል አልገጠማቸውም። ምክንያቱም ክፉኛ ተጎዱ። እግራቸውም እጃቸውም ተመታ። በዚህም ውጊያውን ትተው ወደ ሕክምና እንዲገቡ ተገደዱ።

መጀመሪያ ሕክምና የተደረገላቸው በድሬዳዋ ከተማ ሲሆን፤ የሚቻል ግን አልነበረም። በዚህም ወደ ሐረር ተወሰዱ። ችግሩ በዚህም ቢሆን የሚፈታ አልነበረም። ምክንያቱም ቁስሉ በጣም አመርቅዟል። ሕክምናው ከባድ በመሆኑ ሪፈር መባል ግድ ነውና ወደ አዲስ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

አበባ ተላኩ። ዓመት ያህል ተሰቃይተውም ነው ማገገም የቻሉት። አገራቸው ሁሌም በውስጣቸው ያለች በመሆኗ ከዳኑም በኋላ መቀመጥን ሳይመርጡ በቀጥታ ወደ ሰሜኑ ክፍል በማምራት ጦሩን ተቀላቀሉ።

አገራቸውን እስከሞት ድረስ ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑት እንግዳችን፤ ከጓዶቻቸው ጋር በመሆን ብዙ የፈተና ጊዜን አሳልፈዋል። ይሁን እንጂ ያለባቸው ጉዳት ገና ብዙ ማገገምን ይፈልጋልና ቦታውን ለቀው እንዲወጡ ነገሮች ተመቻቹላቸው። ለዚህ ደግሞ ብርጋዴር ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ የሚባሉ መኮንን እጅግ ጥሩ ነገር ፈጥረውላቸዋል። ሁኔታቸውን ተመልክተው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱም ያደረጓቸው እርሳቸው ናቸው።

በእርሳቸው ምትክ ሌላ ሰው እንዲመጣ ተደረገና በጊዜው ሙሉ አስር አለቃ ስለነበሩ በአዲስ አበባ ሁነው በነበልባል የጦር ክፍል ውስጥ እንዲሠሩ ተደረገ። ወቅቱ ለእርሳቸው ጥሩ እረፍትን የሰጣቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። የተወሰነ ጊዜ በዚህ ከሠሩ በኋላ ደግሞ ወደ ምድር ጦር ተዛውረው በተለያየ ክፍል ውስጥ እንዲሠሩ ሆኑ። ለአብነት ያህል ከሠሩባቸው ክፍሎች ውስጥ የድርጅት መምሪያ ኃላፊ፣ የሹፌር ኮርሱን ጨርሰው ሲመጡ ደግሞ ስምሪት ክፍል ኃላፊ ሆነው የሠሩባቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ።

እስከ 1982 ዓ.ም ድረስ ከውትድርናው መስክ ያልተለዩት ባለታሪካችን፤ የጡረታ እድሜያቸው ሳይደርስ ነው ጡረታ ለመውጣት ፈቃድ የጠየቁት። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአንዳንድ ኃላፊዎች ያልተገባ ጫና እንደነበር ያስታውሳሉ። በተለይም ከሁለት ጄኔራሎች ጋር በምንም መልኩ መግባባት አለመቻላቸው ሥራቸውን እንዲያቆሙ አስገድዷቸዋል።

እርሳቸው ኃይለኛና ለእውነት የቆሙ እንጂ ለማንም የማያጎበድዱ ሰው ናቸው። በዚህም ስህተት ካዩ ‹‹አይሆንም›› ከማለት አይቆጠቡም። ይህ ነገር ያልተመቻቸው ኃላፊዎች ደግሞ ብዙ ተንኮል አሰቡባቸው። በእያንዳንዱ ነገር እየተከተሉም ይኮረኩሟቸው ጀመር። የመጨረሻው የሆነውም ነገሮችን ሁሉ አስበውና አሰላስለው ውሳኔ እንዲሰጡ ያደረጋቸው ነው። ይህም ኃላፊ ሆነው ሳለ በሹፍርናው ተገደው የሄዱበት ጉዞ ሲሆን፤ ከኋላቸው ‹‹እናንተ ጋር እንዲሠራ›› የሚል የዝውውር ደብዳቤ ተልኳልም። ሆኖም ደብዳቤው የደረሰው ቀደም ሲል ያስተማሩት ልጅ ጋር በመሆኑ እርሳቸውን አልጎዳቸውም።

ጭነው የሄዱትን ካራገፉ በኋላና ንብረት መረከቢያው ደብዳቤውን እጃቸው እንዳስገቡ ደስታውን ሊገልጽላቸው የጠራቸው የቀድሞ ተማሪ፤ ነገሩን ሲያስረዳቸው በጣም ደንግጠው እንደነበር አይረሱትም። ነገር ግን ልጃቸው ስለነበር ሁኔታውን በሚገባ አስረዱትና ነገሩ እዚያው አከተመ። እርሳቸውም አዲስ አበባ ተመለሱ። ኃላፊያቸው ጋር ገብተውም ጡረታ መውጣት እንደሚፈልጉ ተናገሩ። ቦርድ መውጣት የሚችሉ ሰው እንደሆኑ ጉዳታቸውን አሳይተው አስረዱ። በጊዜው ኃላፊው ሊቀበሏቸው አልወደዱም ነበር። ምክንያቱም አቅማቸውን በሚገባ ያውቁታል፤ የከፈሉትን መስዋዕትነትም ይረዱታል። ስለዚህም በተሻለ ገንዘብ መውጣት እንዳለባቸው ስላመኑ አይሆንም አሏቸው። ይሁን እንጂ አልበገርም ሲሏቸው ሀሳባቸውን ለውጠው ለጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተጽፎላቸው ውጤቱ እስኪመጣ በዚያው እንዲሠሩ አደረጓቸው። ከውጤት በኋላም ጡረታቸው ተረጋገጠ።

ሥራ በቃኝ የማይሉት ባሻ ዳምጠው፤ ከውትድርናው ቢወጡም ከመሥራት አልቦዘኑም። በዚያ ላይ ጥንካሬያቸውና የሥራ አቅማቸው እንዳለ ስለነበር በብዙ ነገር አግዟቸዋል። እናም በቀጥታ በግለሰብ ደረጃ ተቀጥረው በሹፍርና ማገልገላቸውን አጧጧፉት። በየክፍለ አገሩ የጭነት መኪና ይዘው ያገለግሉም ነበር። መንጃ ፈቃዳቸውን ጎን ለጎን አሻሽለው ደግሞ ከባድ መኪና ያዙ። እስከ ጅቡቲ ድረስ በመሄድም ሥራዎችን ይከውኑ ነበር። አሁን ከሥራ ከለቀቁ አስር ዓመት አልፏቸዋል። በጡረታ ገንዘባቸው ላይ የልጆቻቸው እገዛ ተደምሮበት ጥሩ ኑሮ ያስኖራቸዋል። በብዙ ቤተሰብ የባረካቸውን ፈጣሪን አጥብቀው የሚያመሰግኑት ባሻ ዳምጠው፤ 14 ልጆች፤ 27 የልጅ ልጆች እና 13 የልጅ ልጅ ልጆች አሏቸው። ቅድመ አያት ድረስ ስለዘለቁም ደስተኛ ሆነዋል።



### ከአባት እስከ ልጅ ልጅ

የቀድሞ ሠራዊት ባልደረባ የሆኑት እንግዳችን፤ ውትድርና የትዕግስት መገኛ፣ የሥነ ምግባር መገሪያ፣ በሁሉም ዘርፍ እውቀትን መገብያ ነው ይላሉ። የተፈጥሮ ቦዘኔ ካልሆነ በስተቀር ወታደር ቤትን የቀመሰ ስልጡን የማይሆንበት ምንም ምክንያት እንደማይኖርም ራሳቸውን አብነት አድርገው ያነሳሉ። በተለይም በአገር ወዳድነት ዙሪያ የማይሰበር ማንነት የሚሰጥ እንደሆነ ያምናሉ።

ወታደርነት አርቆ አስተዋይነትን የምንላበስበት ማሕጸን ነው ባይም ናቸው። ለዚህም ምክንያት የሚያደርጉት በሙያው ውስጥ ያለ ሰው ሁሉም እኩል እንደሆነ ያስባል፤ ሁሉም ለአገሩ ይታገላል፤ እስከ ሞት ድረስ መሰዋዕትነትን ይከፍላል ተብሎ የሚታመንበት መሆኑን ነው። በዚያ ደም ላይ ተረማምዶ መክበር የሚታሰብበት ሳይሆን አገርን ወደ ፊት የማስቀጠል ራዕይ የሚሰነቅበትም እንደሆነም ያስባሉ። ይህ ደግሞ ለስሜት ሳይሆን ለሕዝብ እንዲገዛ የሚያደርግ ነው። ቅድሚያ ለራስ ሳይሆን ለአገር የሚያስብልም ቤት ነውም ይላሉ።

ውትድርና በአድር ባይነት የሚገባበትና የሚሠራበት ሳይሆን በፍቅር ተማርኮ በፍላጎት የምንሰማራበት ሙያ ነው። ያ ስለሆነም አባቶቻችን ያልተደፈረች አገርን አስረክበውን የዛሬውን ኑሮ እንድናጣጥመው አድርገውናል የሚሉት ባለታሪካችን፤ ይህና መሰል መለያ ባህሪው ግን አሁን ላይ በብዙ መልኩ ተሸርሽሯል። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ሆዳምነት ነው። ራስ ወዳድነት በማየሉ ምክንያት ውትድርና ሰልጥን እንኳን ሲባል የሚፈራው ጥቂት አይደለም። ሾልኮ የሚወጣውና ገብቶም ራሱን እንጂ አገሩን የማያገለግለው ጥቂት መሆኑን በብዙ መልኩ እያየነው ነው። ለዚህ ደግሞ ባለእዳዎቹ እኛ ነን የሚል እምነት አላቸው።

በምክንያትነት የሚያነሱትም መልካም ወታደር አላፈራንም የሚለው ነው። አገራዊ ማንነትን ሳይሆን የዘር ማንነትን ስላላበስነው በምንም ተአምር አገሩን ወዶ ሕይወቱን ሊሰጣት አልቻለም። ብሔሩ ሲነካ አመመኝ፣ ፈለጠኝ እያለ ይዘላል፤ መሞትና መሰል ነገሮች ማድረግ ምንም እንዳልሆነ ያስባል። ስለዚህም አሁን ያለው ወጣት ሳይሆን እኛ አገር ተረክበን ያልተንቀሳቀስነው መወቀስ ይገባናልም ይላሉ።

ሥራው ምን መሆን እንዳለበት ሳናመላክተው በተሳሳተ ትርክት የሞላነው ወጣት አገሩን ባይወድ ልንገረምበትም አይገባም። ምክንያቱም አገር ሳይሆን ውጪን ናፋቂ አድርገነዋል፤ ያለውን ሀብትም እንዲጠቀምበት አላበረታታነውም። በተለይም ብዙ ታሪክና ብዙ ሀብት እንዳለው አስረድተን ለሁሉም እንደሚበቃ መክረን ሳይሆን ተቃረን፣ ሊወስድብህ ነው እያልነው በምን መልኩ ጎረቤቱን ሊወድና ሊደግፍ ይችላል። እናም እኛ እንጂ እነርሱ ተጠያቂ አይደሉም ባይም ናቸው።

አሁንም ጊዜው እንዳልረፈደ የሚያነሱት እንግዳችን፤ እያንዳንዱን ችግር ለመፍታት አገራዊ ስሜትን ወደሚያቀዳጀው ማህጸን ውስጥ ሁሉም ዜጋ መግባት አለበት። የብሔራዊ የውትድርና አገልግሎትም ሊጀመር ይገባል። ያን ጊዜ አሸናፊነቱ በወሬ ሳይሆን በተግባር ይረጋገጣል። አገር ወዳድነቱን በመስዋዕትነት ጭምር ያሳያል። ስለሆነም እንደ አገር መሠራት ያለበት ከመማር ማስተማሩ እኩል ውትድርናውን መቀላቀል ያስፈልጋል። ሰው ወደ ሕሊናው እንዲመለስም በብዙ መልኩ ያደርገዋልና ነጻነትና እኩልነት እንዲሁም አገር ወዳድነትን ወደሚፈጥረው ቤት ሁሉም ዓይኑን ማማተርም አለበት ይላሉ።

በአሁኑ ሰዓት አገር ላይ ያንዣበባት የውስጥ ጠላት ብቻ አይደለም። የውጪውም ጭምር ነው። ነገር ግን ይህንን የማይረዳ ወጣትና ወታደር በብዙ መልኩ እናያለን። አውቆ ወታደሩ እንዲያፈገፍግ፣ የወታደሩ ሞራል እንዲነካ የሚያደርግም ጥቂት አይደለም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አንድነቱን የሸረሸሩ ነገሮች መፈጠራቸውና ለገንዘብ መስገብገብ መብዛቱ ነው። ስለሆነም ይህንን በሚፈታ መልኩ መንቀሳቀስ ከምንም በላይ ያስፈልገናልም ባይ ናቸው።

እንግዳችን የውትድርና ሙያው ከአባታቸው የተረከቡት ስንቅ ነው። እርሳቸውም ኖረውበት ብዙ ነገራቸውን የገነቡበት ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸውንም ያስተማሩበት ሙያ ሆኗል። ማለትም ሙያውን እንዲወዱት አድርገዋቸዋል። ሁለቱ ልጆቻቸው በሙያው ውስጥ ተሳትፈዋል። አንዱ 20ኛ ኮማንዶር ክፍለ ጦርና ሌላው ስፓርታ ሆኖ በባድሜ ውጊያ እስከመቁሰል ደርሷል። ስለዚህም አገር በውትድርና ሙያ ይገነባል የሚሉትም ለዚህ ነው።

### ወቅታዊ ሁኔታው በእርሳቸው ዓይን

አሁን ከአለንበት ችግር ለመውጣት ከራስ የጀመረ ሥራ ያስፈልጋል። በጉያችን የምንሸሽገው ወንበዴና አገር ሻጭ ሊኖር አይገባም። ፍም እንደያዝን ልንቆጥረው ያስፈልጋል። ምክንያቱም ራሳችንን መጀመሪያ ሳያነደን ሌላው ጋር አይሄድም። እናም መንግሥት ሳይሆን ሕዝብ የበላይ እንደሆነ አስበን ኃያልነታችንን ከራሳችን ማጽዳት መጀመር ይኖርብናል ይላሉ። መምከር የመጀመሪያ ጉዳያችን ሊሆን እንደሚገባም ያስገነዝባሉ። አልመከርም ካለ ደግሞ ከመንግሥት ጋር በመሆን ጥጉን ማስያዝ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። ያን ጊዜ ሆዳሙና አጭበርባሪውን ነጥሎ መምታት እንደሚቻልም ያምናሉ።

የገጠሩ አስተዳደሩን ማረም መጀመሪያ ሕዝብ ከዚያም መንግሥት በብዙ መልኩ ያስፈልገዋል። አጥፊዎች እንዳይመቱ በጊዜያዊ ሆዱ የማይገኙበት ቦታ እየሸሸጋቸው ይገኛልና ይህንን በአንክሮ መመርመር ተገቢ ነው። መጡላችሁ እያለ ቀድሞ የሚነግራቸውን ማስቆም ለመፍትሔው ቁልፍ በር ነው። እናም ሕዝቡ የሚሸሽገውን በመጠቆም መንግሥት ደግሞ ኃላፊዎችን ይዞ ወንጀለኞችን አውጡ በማለት አካባቢውን ማረጋጋት አለበት። በጥቅም የተሳሰረውን በዚህ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በምንም መልኩ ማስቆም አይቻልም እናም ይታሰብበትም ሀሳባቸው ነው።

ሕዝቡ በዚህ ወቅት ለመተንፈስ እንኳን ተጨንቋል። በጎቹ እየተነዱ፣ ሀብት ንብረቱ እየነደደበትና ልጆቹ ጭምር እየተወሰዱበት ዝም ብሏል። ምክንያቱም ተበደልኩ ቢል ለምን ተበደልኩ አልክ ተብሎ ይገደላል፤ አሊያም ለሌላ የከፋ ችግር እንዲጋለጥ ይደረጋል። ለዚህ ደግሞ በመንግሥት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ሰፊውን ቦታ ይይዛሉ። ስለሆነም መንግሥት ነገሩን ማጤንና ያስቀመጣቸውን አመራሮች ተጠያቂ ማድረግ አለበት። ሕዝቡ እፎይታ የሚናፍቅበት ጊዜ ሊሆን አይገባም። በቀደሙት ጊዜያት በአውጫጪኝ ጭምር ነገሮች እንዲረግቡ ይደረግ ነበር። አሁን ግን ምንም መፍትሔ አምጪ ነገሮች አይታዩም። ስለሆነም ይህንን ሊተካ በሚችል መልኩ መሥራትና የሕዝቡን ነጻነት መመለስ ያስፈልጋል ይላሉ።

ሕዝብ አሁን የሚፈልገው የመንግሥትን ድጋፍ ብቻ ነው። አለሁልህ ብሎ ከልቡ ከተነሳ ጠላቱንና ወዳጁን በደንብ ያሳየዋል። የአገርንም ጠላት በሚገባ ማውጣት ይችላል። ቤተሰብ የሚጠይቅበት ሁኔታ ላይ እንኳን አይደለም። እናም የእርስ በእርስ ግንኙነቱንና ቤተሰቡን እንዲሰበስብ ሊያግዘው ይገባልም ባይ ናቸው።

### መልዕክት

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱ ላይ ጥላ ሊያጠላ የሚፈልገውን ሁሉ መስበር አለበት። ምክንያቱም መቼም ቢሆን ኃይላቸው እርሱ ነው። ወኔያቸውም ሆነ ኑሯቸው ከዚያ ውጪ አይሆንም። ስለዚህም በአንድነታቸው ላለመደራደርና ክፍተት ፈጥረው ሌሎች እንዲጠቀሙበት ላለማድረግ ሁልጊዜ መትጋት አለባቸው። ፍርፋሪ የሚበላ ሰው ብዙ ፍላጎት አለው። በአንድ ነገር አይረካምም። አሁን ለውጪው አካል እኛን ለመሸጥ የሚስማማውም ከዚህ አንጻር ነው። ስለሆነም ነቅተን ተው ተመለስ ልንለው ይገባል። ያ ካልተሳካ ደግሞ መቁረጥ ያስፈልጋል የመጀመሪያ መልእክታቸው ነው።

ሌላው ያነሱት ነገር መንግሥት ስልታዊ ሁኔታን እየተከተለ እንደሆነ የተነተኑት ሲሆን፤ እንደተናካሽ ውሻ እዚያም እዚያም ሊዘል አይችልም ይላሉ። አንዱን አጥርቶ መፍታት አለበት። በዚህ መካከል ደግሞ የሚጠፉ ነፍሳት መኖራቸው አይቀርም። የሚያወናብዱ አመራሮች መፈጠራቸውም እንዲሁ። ይህንን ደግሞ ማስተካከል የሚችለው ሕዝቡ በመሆኑ የእኔ ድርሻ ምንድነው ማለት እንዳለ ነው።

# ኢትዮጵያዊ ቤተሰባዊነት ጎልቶ የታየበት የባህል ሳምንት



**መሳኩ ኤርሴ**

የባህል ሳምንት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ብዝሐ ባህል ላለባቸው አገራት ፋይዳው ከፍ ያለ ነው ። ከተለያዩ የባህል ዳራዎች እና ልምዶች ካሉባቸው አካባቢዎች የሚሰባሰቡ ዜጎች እርስ በእርሳቸው እንዲማማሩና ባህሎቻቸውን እንዲጋሩ እድል ይፈጥራል ። ሳምንቱ አንዱ አንዱን እንዲያውቅ እና እንዲማር እድል ስለሚፈጥር ፤ የተለየ ባህል ያለውን እንደ ባዕድ ከማየት ይልቅ ለማወቅ እንዲጓጉ ያደርጋል ። ይህም ማኅበረሰቡን በማስተሳሰር በሕብረ ባህል የደመቀ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ለሚደረገው ጥረት ከፍ ያለ ፋይዳ አለው ።

ካለፈው ዓመት ጀምሮ ኢትዮጵያ የባህል ሳምንት ማክበር የጀመረች ሲሆን፤ ከግንቦት 10 እስከ 16/2013 ዓ.ም ድረስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የባህል ሳምንት በወዳጅነት አደባባይ ተከብሮ ነበር ። ከሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የተወጣጡ ልዑካን ወካይ ቅርሶችን እና የባህል ጭፈራዎቻቸውን ይዘው በመገኘት ያሳዩበት ነበር ። መድረኩ ኢትዮጵያውያን አብሮነታቸው እና ወንድማማችነት የጎላበትም ነበር።

ዘንድሮ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ ዞን በሻሸመኔ ከተማ "ባህላችን ለቱሪዝም ዕድገት" በሚል መሪ ሀሳብ የኦሮሚያ ባህል ሳምንት ተካሂዷል ። በባህል ሳምንቱ ላይ ሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች የባህል ቡድኖች የተሳተፉበት ሲሆን በጎዳና ላይ ትርዒት፣ የባህል ኢንዱስትሪ ምርቶች አውደርዕይ፣ በተለያዩ ሙዚቃ ባንዶች መካከል ውድድር ቀርቦበታል ።

በባህል ሳምንቱ የሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የባህል ልዑካን ቡድኖች የየራሳቸውን አለባበስ እና አጨፋፈርም አሳይተዋል ። ከሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የተለያዩ ብሔሮችን ወክለው የመጡ ቡድኖች ጭፈራዎቻቸውን ለታዳሚው አሳይተዋል ። ከኦሮሚያ ከተለያዩ ዞኖች የመጡ ተወካዮች ደግሞ ከጭፈራ ባሻገር ፣ ባህላዊ ምግቦችን ፣ አልባሳትን ፣ መጠጦችን ለሕዝቡ አስጎብኝተዋል ። የባህላዊ ምግቦቹ እና መጠጦቹ አዘገጃጀት ፣ መቼ እንደሚዘጋጅ ፣ ለማን እንደሚዘጋጅ እንዲሁም ከምን እንደሚዘጋጅ የብሔሩ ተወላጆች ማብራሪያ ሰጥተዋል ።

ከዚያ ጎን ለጎን ሁሉም የክልሉ ዞኖች የተውጣጡ ልዑካን ቡድኖች በአካባቢያቸው የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችን ወካይ ምስሎችን በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ሥራዎችን ሠርተዋል። የቱሪዝም እምቅ ሀብቶችን አሳይተዋል ። በተለያዩ ዘርፎች የመሳተፍ ፍላጎቱ ያላቸው ኢንቨስተሮች መረጃ እንዲያገኙ እድል የፈጠረ ነው ።

የባህል ሳምንቱ የተከበረባት ሻሸመኔ አሳዛኙን ክስተት ካስተናገደች ሁለት ዓመት እንኳ ሳይሞላት አገግማ እንዲህ አይነት ትልቅ መርሐ ግብር ለማስተናገድ መቻሏ በብዙዎች ዘንድ ግርምትን ፈጥሯል ። በወቅቱ የደረሰውን ውድመት ያዩ ሰዎች ከተማዋ ዳግም ለመነቃቃት በርካታ አስርተ ዓመታት ሊፈጅባት እንደሚችል ሲገለጹም ነበር። ሻሸመኔ ግን ከጉዳቷ ለማገገም ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም ። ከተማዋ ፍፁም ሰላም ፣ የተነቃቃች እና ጥሩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚታይባት ሆናለች ። አምራ ደምቃ በአምስቱም በሮቿ እንግዶቿን እያስተናገደች ትገኛለች።

የባህሉ ተሳታፊ የሆኑት እንደተናገሩት ሳምንቱ ኢትዮጵያውያን ያላቸውን የተለያዩ ባህሎችን በአንድ ቦታ ላይ አቅርበው የሚያሳዩበት እድል መፈጠሩ ብዙ ፋይዳ እንዳለው አንስተዋል ። አንዱ የአንዱን እንዲያውቅ እድል የፈጠረ ከመሆኑም ባሻገር ቱሪዝም እና ኢንቨስትመንት ለመሳብም የራሱ ድርሻ ይኖረዋል።

ወይዘሮ ሰላማዊት ሙላቱ፤ ከቢሾፍቱ ባህልና ቱሪዝም የቱለማ ባህላዊ አልባሳት፣ አጨፋፈር፣ አመጋገብ ለማሳየት በቦታው የተገኙ ናቸው። ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የሸዋ ቱባ ባህልን ማስተዋወቅ መቻላቸውን ጠቁመዋል።

የባህል ሳምንቱ የማኅበረሰቦቹ እሴቶች እንዳይረሱ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ። መንግሥት መሰል ትርኢቶች የሚቀርቡበትን መድረኮችን ማዘጋጀቱን መቀጠል አለበት። ለቱሪስት ፍሰት እድል ስለሚፈጥር የኢኮኖሚ እድል የመፍጠር አቅም ስለሚኖረው ትኩረት መድረግ እንዳለበት ጠቁመዋል ። ትርዒቶቹን አሳይቶ ወደ ቤት መሄድ ብቻ ሳይሆን ወደ ገንዘብ መቀየር የሚቻልበትን ሁኔታ መንግሥት በጥናት ላይ ተመርኩዞ ሊሠራበት ይገባል ብለዋል ።

በነዚህ መድረኮች ላይ የታዩ አጨፋፈሮች ፣ አለባበሶች ፣ ምግቦች ፣ መጠጦች የየራሳቸው መገለጫዎችን ቢኖሩም የሚያቀራርባቸው ነገሮችም አሉ ። ይህም የኢትዮጵያውያን በዘመናት አብሮነት ሂደት የገነቡትን ትስስር አመላካች ነው ። በመድረኩ ሲዳማን ወክሎ የተሳተፈው አስናቀ አየለ እንደሚለው፤ የአንዳንድ ብሔሮች ባህላዊ ምግብ መመገቢያ ቁሶች የሚታየው መመሳሰል የሕዝቦችን ትስስር የሚያመላክት ነው ።

እንደ አቶ አስናቀ ማብራሪያ ፤ በባህል ሳምንቱ የቀረበውን የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦችን መገለጫዎችን ለማየት እድል የፈጠረለት እንደመሆኑ ሙሉ ኢትዮጵያን በአንድ ቦታ የማየት እና ስለ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከዚህ በፊት ከሚያውቀው የበለጠ የማወቅ እድል አግኝቷል። ሲዳማ ሆኖ የመላውን ኢትዮጵያውያንን አመጋገብ፣ አለባበስ፣ አጨፋፈር እና ሌሎች መገለጫዎች ማወቅ መቻሉ በየትኛውም አካባቢ ቢሄድ እንግድነት እንዳይሰመው እንደሚያደርገው ያነሳል ።

በተመሳሳይ መልኩ ከሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች በባህል ሳምንቱ ላይ የተገኙ ሲዳማ ክልልን የማያውቁ ኢትዮጵያውያን ሲዳማ ሳይሄዱ በሻሸመኔ ሆነው ስለ ሲዳማ እንዲያውቁ እድል መፍጠሩን ተናግሯል ። በቀጣይ በርካቶች ሲዳማ ሄደው ለመጎብኘት ጉጉት እንዲያድርባቸው የሚያደርጉ እሴቶች መታየታቸውን ጠቁሟል።

የብሔረሰቦችን ባህሎችን ከማወቅ ባሻገር ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከተገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በግል የመተዋወቅ እድል እንደተፈጠረለት የሚናገረው አስናቀ ፤ ከተለያዩ አካባቢዎች ከመጡ ኢትዮጵያውያን ጋር ጓደኝነት ለመፍጠር እንዳስቻለው አብራርቷል ። ይህም ለወደፊት ሕይወቱ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ያነሳል ። በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ ቢሄድ ብቸኝነት እንደማይሰማው የሚያደርግ መሆኑን አንስቷል ።

አገር ለማልማትና ሰላምን እውን ለማድረግ መተዋወቅ እና መቀራረብ ወሳኝነት አለው። አንዱ ሕዝብ የሌላውን ቋንቋ ፣ ባህል እና ሌሎች መገለጫዎችን እንዲያውቅ እድል ይፈጥራል። ማኅበረሰቡ የሚታወቅበትን ተቻችሎ የመኖር ባህሉን እንዲያጠናክር ስንቅ በመሆንም ያገለግላል። ይሄ እንደ ቀላል መርሐ ግብር የሚታይ አይደለም ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩ መረጃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት ተዋደው በኖሩ በብሔር ብሔረሰቦች መካከል አብሮነትና መቀራረብን ሳይሆን ልዩነትን፤ ጥላቻን የሚሰብኩ እየሆኑ መምጣታቸውን የሚያነሳው አቶ አስናቀ ፤ ኢትዮጵያውያን በማኅበራዊ ሚዲያው ላይ በሚናፈሰው አፍራሽ ወሬዎች እንዳይወሰዱ የባህል ሳምንትን የመሳሰሉ መርሐ ግብሮች ከፍ ያለ ጥቅም እንዳላቸው ያብራራል ።

የባህል ሳምንቱ ከምስራቅ ፣ ምዕራብ፣ ከደቡብ ሰሜን ጫፍ የሚመጡ ሕዝቦች መገለጫዎቻችን የሚያሳዩበት በመሆኑ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ በአገሪቱ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች አንዱ አንዱን እንዲጠላ እንዲጠራጠር፣ እንዲሸሽ የሚገፋፉ እኩይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች የሚያናፍሱትን አደገኛ ትርክት ለማክሸፍ ትልቅ መድረክ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው ። ይህም ኢትዮጵያዊነት እየጠነከረ እና አንዱ አንዱን የመረዳት እድል እየሰፋ እንዲሄድ የሚያስችል ነው ።

ኢትዮጵያውያን የሚገናኙበት የባህል ሳምንታት በተደጋጋሚ ቢዘጋጁ ኢትዮጵያውያን እንዲተዋወቁ እና እንዲቀራረቡ እንዲሁም አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ እድል የሚፈጥር እንደመሆኑ በቀጣይነት በአገር አቀፍ እና በክልሎች ደረጃ ቢዘጋጁ ከፍ ያለ ፋይዳ እንደሚኖረውም ተናግሯል ።

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰዓዳ ኡስማን እንደተናገሩት ፤ ከዚህ ቀደም የኦሮሚያ ባህል ሳምንት የክልሉን ዞኖች ብቻ ባሳተፈ መልኩ ይከበር ነበር። በዚህ ዓመት ግን ሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦችን ባሳተፈ ሁኔታ የሁሉም ክልሎች ባህል ቡድኖች በተገኙበት እንዲሁም የሁሉም ክልሎች ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት መከበሩ ለበዓሉ ውበትና ድምቀት ጨምሯል ። የዘንድሮ የባህል ሳምንት ኢትዮጵያውያን ብዙ ሆነው እንደ አንድ የታዩበት ነው ።

ሻሸመኔን እና የአርሲን ሕዝብ በማይገልጽ መልኩ ከባድ ጉዳት አስተናግዳ የነበረችበት ነው ። ከተማዋ ግን በሕዝቦቿ እና በመንግሥት ጥረት ሁለት ዓመት ሳይሞላት የወደመውን ጠግና ፣ የፈረሰውን መልሳ ገንብታ መገኘቷ የሚያስመሰግናት ነው ። ዳግም ወደ ነበረችበት ለመመለስ እስከ 50 ዓመት ሊፈጅባት ይችላል የተባለችው ሻሸመኔ በሁለት ዓመት ውስጥ ማገገም መቻሏ ሕዝብና መንግሥት እጅ ለእጅ ተያይዘው ከተንቀሳቀሱ የማያሳኩት ነገር እንደማይኖር የሚያሳይ ነው ብለዋል።

የባህል ሳምንት መዘጋጀቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም እንዳለው የጠቆሙት ወይዘሮ ሰዓዳ የውጭ እና የአገር ውስጥ ቱሪስቶችን ለመሳብ እንዲሁም ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋት እድል እንደሚፈጥር ተናግረዋል ። እምቅ አቅም የታየበት እንደመሆኑ የውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ወደ አገር ውስጥ እንዲሳቡ ያደርጋል ። ያልታዩ የባህል ሀብቶችና ጸጋዎች የታዩበት እንደመሆኑ ባህልን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ከሚኖረው ፋይዳ ባሻገር ኢንቨስትመንት እድገት ከፍተኛ ሚና ይኖዋል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው ፤ "ባህል ሰፊና ትልቅ ትርጉም ያለው የአንድ የኅብረተሰብ ማንነት የሚገለጽበት ምሰሶ ነው" ሲሉ የገለጹ ሲሆን ባህልን መጠበቅ ፣ መንከባከብ እና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው።

ኢትዮጵያ ህብር ባህል ያለባት አገር እንደመሆኗ ባህሎችን ማስተዋወቅ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ የሚገባው ቢሆንም እስካሁን ድረስ በሚገባው ልክ አልተሠራም ብለዋል ። ባለፈው ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው የባህል ሳምንት አከባበር መልካም ጅምር የታየበት ነበር ብለዋል ።

የባህል ሳምንቱን በክልሎች እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ማክበር ፋይዳው የጎላ መሆኑ ስለታመነበት በቀጣይ የባህል ሳምንቶች እንዲከበሩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል ። የባህል ሳምንቱን በኢትዮጵያ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካ ደረጃም ማክበር የቀጣናውን ህዝቦች አብሮነት ለማጠናከር ስለሚረዳ ፤ በዚህ ወር መጨረሻ በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ በአዲስ አበባ የባህል ሳምንት ለማክበር ቀጠሮ እንደተያዘለት ነው የጠቆሙት።

በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ የሚካሄደው የባህል ሳምንት በዓይነቱ ልዩ የሆነ የምስራቅ አፍሪካ የባህልና ኪነጥበብ ሲምፖዚየም ከመላው አፍሪካ የተውጣጡ የባህል ዘርፍ ያሉ ሚኒስትሮች፣ የታወቁ የአፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች፣ ከምስራቅ አፍሪካ የተውጣጡ የባህል ቡድኖች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንደሚሳተፉበትም አቶ ቀጄላ ገልጸዋል።

የበዓሉ አከባበር ሥነ-ሥርዓት ላይ ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎች፣ ሃደ ሲንቄዎች፣ የሻሸመኔ ከተማ ነዋሪዎች በፌስቲቫሉ ታድመዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የኢትዮጵያውያን አሻራ ግድብ ጅማሮ

**ዋስልኝ አየለ**

የዚህ ሳምንት «ሳምንቱ በታሪክ» በአንድ ቀን ሁለት ክስተቶች ላይ ያተኩራል፤መጋቢት 24 ላይ። ክስተቶቹ የሰባት ዓመታት ልዩነት አላቸው።

የመጀመሪያው ክስተት ኢትዮጵያውያን በአንድ ሳምባ የተነፈሱበት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት 11ኛ ዓመት ነው። ዕለቱ ቅዳሜ ነበር፤ እነሆ ዘንድሮም መጋቢት 24 ዕለተ ቅዳሜ ላይ ውሏል። በወቅቱ ምን ተባለ የሚለውን ክስተት እንዲህ እናስታውሰው!

ዕለተ ቅዳሜ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ረፋድ፤ በያኔው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በአሁኑ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ለመላው ኢትዮጵያውያን አንድ ታላቅ ብስራት ተበሰረ። አገራዊ አቅምን የሚያሳይ፣ የተፈጥሮ ሀብት ፍትሐዊ ክፍፍልን የሚያረጋግጥ፣ ሰላም እና መተባበርን የሚመሰክር፣ ሕዝባዊ ጥቅምን የማሳየት ዓላማ ያለው፣ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የጥረት አሻራ የሚታተምበት፣ አገር በአንድ ልብ የሚያስብበት በአንድ ሳምባ የሚተነፍስበት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሊገነባ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ።

ይህ በኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ የሆነ የህዳሴ ግድብ እንደሚገነባ ተበሰረ። ይህን ለዘመናት የማይደፈር መስሎ የኖረን ዓባይ የቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ መሪነት ተደፈረ። በትናንትናዋ ዕለት ቅዳሜ፣ በትናንትናዋ ቀን 24፣ በዛሬዋ ወር መጋቢት ግን በያኔው ዓመተ ምህረት 2003 ይህ ብስራት ተነገረ።

የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመሠረት ድንጋዩን ሲያስቀምጡ እንዲህ አሉ። « ... የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላብ ፊርማ ያረፈበት ግድብ በመሆኑ የህዳሴ ጉዟችን መሐንዲሶች እኛው፣ ግንበኞቹና ሠራተኞቹ እኛው፣ የፋይናንስ ምንጮችና አስተባባሪዎች እኛው፣ በአጠቃላይ የህዳሴ ጉዟችን ባለቤቶች እኛው መሆናችንን የሚያሳይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታችን ነው።» ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በኋላ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላቡን ፊርማ በማሳረፍ፣ መሐንዲስ፣ ግንበኛና ሠራተኛ፣ የፋይናንስ ባለቤት መሆኑን አረጋገጠ።



የመንግሥት ሠራተኛው ከደመወዙ፣ ነጋዴው ከወረቱ፣ ገበሬው ከምርቱ፣ ተማሪው ከደብተርና እስኪሪቢቶው ወጪውን በመቀነስ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የህዳሴው ግድብ ባለቤት መሆኑን አስመሰከረ። በዓባይ ጉዳይ ላይ ለዘመናት ሲንከባለሉ የኖሩ ጥያቄዎች ምላሽ አገኙ። በቅኝ አገዛዝ ዘመን ዓባይ በኢ-ፍትሐዊ ቦይ እንዲፈስ የተወሰነባቸው ውሳኔዎች በዚያች ዕለት በዚያች ቀን ዋጋ እንደሌላቸው ተረጋገጠ። ስሙ ብቻ የተረፋቸው የናይል ተፋሰስ አገሮች አንድም በኢኮኖሚ አቅም ማጣት አንድም በአውሮፓውያን ኢ-ፍትሐዊ ውሳኔ ከደጃቸው ለሚፈሰው ዓባይ ለበርካታ ዘመናት የበይ ተመልካች ሆነው ኖረዋል። ዳሩ ግን የቅኝ አገዛዝ ዘመን አክትሞ፣ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ዘመናቸው አለፈና ዓባይ በፍትሐዊ ቦይ እንዲፈስ ተወሰነ።

ዓባይ በወኔ እና በቆራጥነት እንደሚገነባ የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ በቆራጥ ወኔ ተናገሩ። ያኔ ባረጀ እና ባፈጀ አገዛዝ የነበረው አመለካከት ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው ወኔያቸውን አሳዩ። እስኪ በፓርላማው ውስጥ ከተናገሩት ንግግር ደግሞ ይችን እንውሰድ። «አንዱ የግብፅ ስትራቴጂ ያው ትልቅ ወታደር አስቀምጦ ማስፈራራት ነው፤ ይህን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባ ፖሊሲ ቢኖር አለመፍራት ነው።» ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በኢትዮጵያውያን እውን ሆነ። ግብፅ በየጊዜው የምታነሳው እንጉርጉሮ ግድቡን ለሰከንድም እንደማያስቆመው ዳግም ተረጋገጠ። ኢትዮጵያ ሰላማዊ ውይይትን ለዓለም አሳየችበት።

ከዚች ዕለት ጀምሮ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኔ እያለ የሚጠራው ሆነ። ዓባይ የጋራ መግባቢያ፣ የጋራ ማሰቢያ፣ የጋራ ሀብት ሆነ። ኢትዮጵያ በራሷ አቅም አትገነባውም የሚለው የውስጥ ለውስጥ ሹክሹክታ አንድምታ ሳያገኝ ቀረ። በዓባይ ጉዳይ የመጣ ነገር ሁሉ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ በመሆኑ በጋራ ማዳመጥ ሆነ።

የመገናኛ ብዙኃን ስለ ግድቡ የሚያወሩት ወሬ በሁሉም ሰው ልብ በአንዴ መድረስ ቻለ። ምክንያቱም ስለ ዓባይ ምን ተባለ የሚለው ነገር የሁሉም ሰው ጉጉት ስለሆነ። ይህ ኢትዮጵያንን በአንድ ቋንቋ ያነጋገረ ዓባይ በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ የደስታ ምንጭ በመሆን ኲራትን ፈጠረ። ለበርካታ ኢትዮጵያውያንም የሥራ ብቻ ሳይሆን የጥበብ ምንጭ ሆነ። ከተማሪ እስከ ተመራማሪ በዓባይ ላይ ቅኔ በመቀኘት መጠበብ ጀመሩ። ከትምህርት ቤት ሚኒሚዲያ እስከ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በዓባይ ላይ ምን እንጠበብ በሚል ውስጣቸውን ጠየቁ። በየመድረኮች ዓባይን የሚያመሰግኑ ስንኞች፣ ዓባይን የሚያስውቡ ዜማዎች ተፈጠሩ። ይህም ለበርካታ ወጣቶች እና ተማሪዎች የጥበብ የፈጠራ ምንጭ ሆነ።

ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከደለል ለመከላከል ሲባል ለበርካታ አርሶ አደሮች ሌላ አጋጣሚ ፈጠረ። ይህም አርሶ አደሮቹ የሚሠሩት እርከን ዓባይን ብቻ ሳይሆን የአርሶ አደሮችን የእርሻ ማሳም አፈሩን በማስቀረት በውሃ እንዳይሸረሸር እስከ ማድረግ ደረሰ።

የመገደቡ ብስራት የተነገረው ዓባይ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ሌላ የይቻላል መንፈስን እና ወኔን ፈጠረ። እንዲያ በአስፈሪነቱ ይመለክበት የነበረው ዓባይ ለካ እንዲህ በሰው ልጅ ቁጥጥር ሥር መዋል ይችላል? የሚል የይቻላል በራስ መተማመንን ፈጠረ። በቃ! የሰው ልጅ የቱንም ነገር መሥራት ይችላል አሰኘ። ግድቡ ከተጀመረ በኋላ ዓባይ የመታየት እና የመጎብኘት ዕድሉ እየጨመረ፤ በስም ብቻ ያውቁት የነበሩ በርካታ ከተሜዎች ዓባይን በአካል ሄዶ የማየት ጉጉት አደረባቸው። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የግድቡ ሥራ ከ84 በመቶ በላይ ተከናውኖ ሲታይ እንኳን የግድቡ ባለቤት የሆነውን ኢትዮጵያዊ ይቅርና ይህን ከዓለማችን ግዙፍ ፕሮጀክቶች አንዱ የተባለለትን ግድብ ማንም የማየት ጉጉት ያድሮበታል።

ያኔ ሲጀመር 5250 ሜጋ ዋት ያመነጫል ተብሎ የታሰበው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አቅሙን አሳድጎ ከፍ አድርጓል። ይህ መላው ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመላው ዓለም ሰላም እና አንድነትን እየመሰከረ ያለ ታላቅ ግድብ ሲጠናቀቅ የዓለምን ቀልብ በመሳብ ኢትዮጵያ የዓለም የሰላም ተምሳሌት መሆኗን በተግባር ያረጋግጣል። እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን የሚለው መሪ ቃል ይፈፀምና ሌላ እንድንጀምር ማሳያ ይሆናል።

በዚህ ዓመት ደግሞ ኃይል በማመንጨት ሥራውን ጀምሯል። በአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደተነገረው፤ ይህ የኢትዮጵያውያን አሻራ የሆነው ግድብ የትውልድ ቅብብሎሽ ነው። ያሰቡትንም፣ የጀመሩትንም፣ እያስፈጸሙት ያሉትንም እናመሰግናለን!

## የዶክተር ዐቢይ አሕመድ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሹመት

ሌላኛው የዚህ ሳምንት ክስተት በዚሁ በመጋቢት 24 ቀን የተከናወነው የዶክተር ዓቢይ በዓለ ሲመት ነው። የዶክተር ዐቢይ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት መምጣት የኢትዮጵያን የፖለቲካ እንቅስቃሴ አዲስ ድባብ አላበሰው። «ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በቁሩ» ይባል የነበረው ተቀየረ። መንግሥትን ለመቃወም ሰልፍ ይወጣባቸው የነበሩ አደባባዮች መንግሥትን ለመደገፍ በሚወጣ ሰልፈኛ ተጥለቀለቁ።

ዶክተር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ማግስት ጀምሮ በተለያየ ዘርፍ ውስጥ የሚገኘውን የማኅበረሰብ ክፍል ማወያየት ጀመሩ። መምህራንን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ የኪነ ጥበብ ሰዎችን፣ ባለሀብቶችን... በየደረጃው ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል አወያይተዋል። በተለያዩ አካባቢዎች እየሄዱም ነዋሪውን አወያይተዋል።

እንዲህ እንዲህ እያለ የቀጠለው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጉዞ እዚህ ደርሶ እነሆ ዛሬ እየታወሰ ነው። በተለይም በበዓለ ሲመታቸው ቀን በፓርላማ ያደረጉት ንግግር ዛሬ ድረስ በተለያዩ ዓውዶች ይጠቀሳል። ይህን ታሪካዊ ንግግር እነሆ በሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን እናስታውሳችሁ!

“...አገራችን ኢትዮጵያ በመንግሥት አስተዳደር ሥርዓቷ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በምታከናውንበት በዚህ ታሪካዊ ቀን በተከበረው ምክር ቤት ፊት ቀርቤ ይህን ንግግር ለማድረግ ስለበቃሁ የተሰማኝን ልዩ ክብር ለመግለጽ እወዳለሁ። ከሁሉ አስቀድሜ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአገራችን ለተከሰተው ፖለቲካ አለመረጋጋት የመፍትሔ አካል ለመሆን፣ የአገር ክብርና ብሔራዊ ጥቅም በተሻለ ሁኔታ በአዲስ አመራር ሊጠበቅ ይችላል ብለው በማሰብ፣ ለአኅጉራችን ምሳሌ በሆነ መልኩ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ላሸጋገሩት ለክቡር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከፍ ያለ አክብሮቴን እገልጻለሁ። በተመሳሳይ የመንግሥታዊ ሥልጣን ሽግግሩ ያለ እንከን እንዲከናወን ልዩ ሚና ሲጫወቱ ለቆዩት ሁሉ በመላው ሕዝባችን ስም ከልብ አመሠግናለሁ።



### ዕለቱ ለአገራችን ታሪካዊ ቀን ነው!

በታሪካችን በተለያዩ አጋጣሚዎች አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የመጀመር ዕድሎችን አግኝተን ብዙዎቹን በወጉ ሳንጠቀምባቸው አምልጠውናል። አሁንም ይህ የሥልጣን ሽግግር አዲስ ምዕራፍ የምንጀምርበት ሌላ ታሪካዊ ዕድል ነው። በመሆኑም በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ልንጠቀምበት ይገባል።

ኢትዮጵያ ማህፀነ ለምለም ናት። ከፍ ባለ የአገር ፍቅር መንፈስ ሁሌም የሚተጉ ልጆችን አፍርታለች። ልጆቿም ወደ ቀድሞ ክብሯ እንድትመለስ፣ የሕዝቧ ሰላምና ፍትሕ እንዲጠበቅ፣ ብልፅግና ያለ አድልኦ ለመላው ዜጎች ይዳረስ ዘንድ አጥብቀው ይመኛሉ. . . ይደክማሉ። በአገር ውስጥና በውጭ ሆነው ስለአገር አንድነትና ሰላም፣ ስለፍትሕና እኩልነት እንዲሁም ስለብልፅግና ይጮሃሉ፣ ይሞግታሉ፣ ይሟገታሉ። ይህ የሥልጣን ሽግግር ሁለት ዓበይት እውነታዎችን የሚያመላክት ነው። ክስተቱ በአንድ በኩል በአገራችን ዘላቂ፣ የተረጋጋና ሁሉን አቀፍ የሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረት ስለመጣላችን ማሳያ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜው ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ጋር እኩል የሚጓዝና በሕዝብ ፍላጎት የሚገዛ፣ ሕዝብን አለቃው አድርጎ የሚያገለግል ሥርዓት እየገነባን መሆኑን ያመለክታል።

### ወቅቱ ከስህተታችን ተምረን አገራችንን የምንክስበት ወቅት ነው

መሪ ድርጅታችን ኢሕአዴግ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመሩን አጥብቆ በመያዝ አገራችንን ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ ባስተዳደረበት ወቅት፣ በሁሉም መስክ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ሕገ መንግሥታዊና ፌዴራላዊ ሥርዓት ገንብቷል። ዓለም በአንድ በኩል በጥሞና፣ በአግራሞትና በጉጉት በሌላ በኩል ደግሞ በሥጋት እየተመለከተው ያለ አገራዊ ለውጥ ላይ እንገኛለን። ያሳካናቸው በርካታ ድሎች እንዳሉ ሁሉ በፍጥነት መቀረፍ የሚገባቸው በርካታ ጉድለቶች እንዳሉም እናምናለን። ከስህተቶቻችን ተምረን ወደፊት በመራመድ ማተኮር ያለብን ጉዳይ የተሻለች አገር ለሁላችንም በመገንባቱ ላይ ነው። ዋናው ቁም ነገር አገራችንን ከፍ ወዳለ ምዕራፍ ማሸጋገሩና አንድነቷን ጠብቃ የምትቀይበትን ሁኔታ በቀጣይነት እያረጋገጡ መሄዱ ነው። ኢትዮጵያዊነት ያስተማረን እውነታ በጊዜያዊ ችግሮች ተሸንፎ መውደቅን ሳይሆን፣ ፈተናዎችን ወደ ዕድልና መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ድል መቀዳጀትን ነው።

ትናንት አባቶቻችን በመተማ፣ በዓድዋና በማይጨውና በካራማራ አጥንታቸውን ከስክሰው የከበረ ደማቸውን አፍስሰው በክብርና በአንድነት ያቆዩዋት አገር አለችን። እኛ ዕድለኞች ነን። ውብ አገር አኩሪ ታሪክ አለን። እኛ መነሻችንን እናውቃለን። በርካታ ዘመናትን የሚሻገር ታሪክ ያለው ታላቅ ሕዝብ ነን። ኅብረታችንን ለዓለም ምሳሌ መሆን ይችላል። ጠላቶቻችንን አንበርክኳል። ሉዓላዊነታችንን ጠብቆ ዛሬ ላይ ከማድረሱም በላይ፣ ለሌሎች ሕዝቦችም የነፃነት ትግል አርዓያ ሆኗል።

ማንነታችን እንዳይለያይ ሆኖ የተሰናሰለ፣ እንዳይነጣጠል ሆኖ የተገመደ፣ የተዋደደና የተዋሀደ ነው አማራው በካራማራ ለአገሩ ሉዓላዊነት ተሰውቶ የካራማራ አፈር ሆኖ ቀርቷል። ትግራዋይ በመተማ ከአገሬ በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ሆኗል። ኦሮሞው በዓድዋ ተራሮች ላይ ስለአገሩ ደረቱን ሰጥቶ የአገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከዓድዋ አፈር ተቀላቅሏል። ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤኒሻንጉሉ፣ ወላይታው፣ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሐዲያውና ሌሎቹም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በባድመ ከአገሬ በፊት እኔን ብለው እንደወደቁ ከባድመ አፈር ጋር ተዋህደዋል። አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት እኛ ስንኖር ሰዎች፣ ስናልፍ አፈር፣ ስናልፍ አገር እንሆናለን። የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ክቡር ሥጋና ደም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ሆኖ ታገኙታላችሁ። ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያዊ እንሆናለን።”

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## "ልጆቼ እኔን መብለጥ አለባቸው ፤ ከበለጥኳቸው ግን አገሪቱ ቆማለች ማለት ነው"

- አርቲስት ጥላሁን ዘውገ



**ዱላው እንዳልቀረለት ሲያውቅ ደብተሩን ይዞ ወጥቶ ከሌሎች ተገራፊዎች ጋር ተንበረከከ። ተነስ ተነስ አሉ መምህሩ። የጻፈውን እንዲያነብ ተነገረው። ድርሰቱ ጥሩ ስለሆነ ሳይሆን ድርሰት እንዴት እንደማይጻፍ ለተማሪዎች ሊያሳዩበት እንደሆነ በማሰብ በጭንቀት የጻፈውን አነበበ። አጨብጭቡለት ተባለ። ያኔ መምህሩ ድርሰቱን እንደወደዱት አወቀ። በኩራት ልቡ ተሞልቶ ተገራፊ ጓደኞቹን ወደኋላ እየገረመመ ወደቦታው ተመለሰ**

**አቤል ገ/ኪዳን**

ቀጠሮአችን መኖሪያ ቤቱ ነበር።ስንደርስ አንዲት ክፍል ውስጥ ከአንድ የሥራ ባልደረባው ጋር ሆነው የቀረጹትን ማስታወቂያ አርትኦት እየሠሩ ነው። የቤቱ መገኛ ፈረንሳይ ለጋሲዮን 41 ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ ነው። ተራራማ የሆነ ቦታ ላይ የተሠራው ቤቱ አካባቢውን እና የአዲስ አበባን የተወሰነ ክፍል ማሳየት ይችላል።ለእይታ ምቹ ሆኖ የተሠራ ቦታ ላይ ወንበር ይዘን ተቀመጥን።ወግ አዋቂ ነው።አንደበቱ ለዛ አለው።የዛሬው እንግዳችን ለሦስት አስርተ ዓመታት ገደማ በኢትዮጵያ ሕዝብ አይን ውስጥ የኖረው ተዋናይ እና የማስታወቂያ ባለሙያ አርቲስት ጥላሁን ዘውገ ነው።

የተወለደው የዛሬ 55 አመት ታህሳስ 1 ቀን 1959 ኢ.ም አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነው።አባቱ መቶ አለቃ ዘውገ ወልደሩፋኤል ወታደር ነበሩ።በጃንሆይም በደርግም ዘመን አገራቸውን በውትድርና አገልግለዋል።እናቱ የቤት እመቤት የሆኑት ወ/ሮ ለገሴ ጸጋዬ ይባላሉ።ሁለቱ ሰዎች ከወለዷቸው ስድስት ልጆች መሐከል ጥላሁን ሁለተኛ ልጅ ነው። ቤተሰቡ ውስጥ ከሱ ቀድሞ የኪነ ጥበብ ዝንባሌ ያለው ሰው አልነበረም።ነገር ግን የተወለደበት እና እትብቱ የተቀበረበት ፈረንሳይ ለጋሲዮን አርቲስቶችን በማፍራት የታወቀ ነው።ስለዚህም በቤቱ ውስጥ የኪነ ጥበብ ዝንባሌ ባይኖርም የአካባቢው የጥበብ መንፈስ ጥላሁንም ዳብሶት ነበር።እነ ጥላሁን ገሰሰ ፤ እነ ሙናዬ መንበሩ ፤ እነ ተፈራ ካሳ ፤ እነ ሳህሌ ደጋጎ ፤ እነ ለማ ገብረ ህይወት ፤ እና ሌሎችም እውቅ አርቲስቶች የኖሩበት ሰፈር በጥላሁን ላይም ጥላ ቢጥል አይገርምም።

ጥላሁን እና ኪነ ጥበብ የተገናኙበት መንገድ አስገራሚ ነው።የሚማርበት ትምህርት ቤት ራስ ስዩም (በኋላ ሕዝባዊ ሠራዊት ትምህርት ቤት የተባለ) የ6ኛ ክፍል ተማሪ እያለ በክፍላቸው በደረጃ ከአንድ እስከ ስድስት የወጡ እና የደህና ቤተሰብ ልጅ በመሆናቸው ለድራማ የተመረጡ ተማሪዎች ስለ ቀድሞው የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ችግር የሚያወራ ድራማ እንዲሠሩ ተመርጠው ነበር።ድራማውን የሚለማመዱት ደግሞ ከትምህርት ክፍል ጊዜዎች በአንዱ ከክፍል ወጥተው ሌላ ባዶ ክፍል ሄደው ነው።ስለዚህም አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መዝለል ነበረባቸው።የተዘለለው ክፍል ጊዜ የእንግሊዝኛ ክፍለ ጊዜ ነው።

የእንግሊዝኛ መምህሩ ቁጡ ናቸው። ለመግረፍ ይበረታሉ።ጥላሁን ደግሞ የቤት ሥራ መሥራት አይሆንለትም። ደግሞም የዚያን ቀን የቤት ሥራ አልሠራም።ስለዚህም የዚያን ቀንም ዱላ ይጠብቀዋል። ያን ዱላ ለማምለጥ ያለው ብቸኛ አማራጭ ድራማ ሠሪ ባይሆንም ድራማ ሠሪዎቹን ተከትሎ መውጣት ነው። ወጣ። ድራማ ሠሪዎቹ ልምምድ ወደሚያደርጉበት ክፍል ሲሄዱ ጥላሁን አውላላ ሜዳ ላይ ቀረ። ደጅ መገኘት ሌላ ቅጣት ያስከትላል።ወደ ሽንት ቤት መሄድ ጀመረ።ወደዚያ ሲሄድ ደግሞ ሌላ ችግር ተፈጠረ። ዩኒት መሪው ወደዚያ እየመጡ ነው።ከተያዘ ሌላ ቅጣት ይከተለዋል።ግራ ገባው።ድራማ ሠሪዎቹ ጋር እንዳይገባ አይፈልጉትም።ክፍል እንዳይመለስ ዱላ ይጠብቀዋል።ደጅ እንዳያውደለድል ዩኒት መሪው አሉ።

ግራ ገብቶት ሲቁለጨለጭ አንድ አጋጣሚ ተከሰተ።ድራማ ሠሪዎቹ ጭቅጭቅ ጀመሩ።የጭቅጭቁ መንስኤ ደግሞ ድራማው ላይ ሁሉም ሰው ዘበኛ ሆኖ ለመሥራት አለመፈለጉ ነው።ጥላሁን ይሄን አጋጣሚ ማባከን አልፈለገም።እኔ ዘበኛ ልሁንላችሁ አላቸው ፤ ተስማሙ ፤ ተዋናዮቹን ተቀላቀለ ፤ ዱላውን አመለጠ። ድራማው ተሠርቶ ለተማሪዎች ሲቀርብ ተወዳጅነትን አገኘና ከአራቱ የስድስተኛ ክፍል ንዑስ ክፍሎች የነ ጥላሁን ክፍል አሸናፊ ሆነ።ለማሸነፉ ደግሞ ዋነኛው መንስኤ የዘበኛው አስቂኝ ገጸ ባህሪ ሆነ።ጥላሁን ዝነኛ ሆነ።እኒያ የሚፈራቸው መምህር እንኳን ጥላሁንን ወደዱት።ከዚያ ወዲያ ገርፈውትም አያውቁ።ጥበብ ጥላሁንን ከተገራፊነት አውጥታ የራሷ አደረገችው።

ቀጠለ።በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ሌላ ክስተት ተከሰተ።አማርኛ መምህሩ ዓርብ እለት ሁሉም ሰው 10 መስመር ድርሰት ጽፎ እንዲመጣ አዘዙ።የቤት ሥራው የሚቀርበው ሰኞ ነው።ቅዳሜና እሁድ በጨዋታ ታልፎ ጥላሁንም የቤት ሥራውን ሥራ ሳይሠራ ሰኞ ደረሰ።ሰኞ ጠዋት መምህሩ ክፍል እንደገቡ የቤት ሥራውን አውጡና ጠረጴዛ ላይ እንዲያስቀምጥ አዘዙ።ጥላሁን የቤት ሥራውን እንዳልሠራ ሲያውቅ ክው አለ።ነገር ግን ላለመገረፍ የአቅሙን መላ ዘየደ። ቀጭን እና ረዥም እንደመሆኑ እሱ ከኋላ ነው የሚቀመጠው።ስለዚህም መምህሩ ከፊት ጀምረው የእያንዳንዱን ተማሪ የቤት ሥራ እያዩ ያልሠራውን ለዱላ ሲያስወጡ ጥላሁን መጻፍ ጀመረ።

ከዱላው ስለማምለጥ እንጂ ስለ ድርሰቱ ጥራት አላሳሰበውም፤ጻፈ።እሱ ጋር ሲደርሱ በደመነፍስ የሞነጫጨራትን ድርሰት አቀረበ።አነበቡት።ያዝና ውጣ አሉት።ዱላው እንዳልቀረለት ሲያውቅ ደብተሩን ይዞ ወጥቶ ከሌሎች ተገራፊዎች ጋር ተንበረከከ።ተነስ ተነስ አሉ መምህሩ።የጻፈውን እንዲያነብ ተነገረው። ድርሰቱ ጥሩ ስለሆነ ሳይሆን ድርሰት እንዴት እንደማይጻፍ ለተማሪዎች ሊያሳዩበት እንደሆነ በማሰብ በጭንቀት የጻፈውን አነበበ።አጨብጭቡለት ተባለ።ያኔ መምህሩ ድርሰቱን እንደወደዱት አወቀ።በኩራት ልቡ ተሞልቶ ተገራፊ ጓደኞቹን ወደኋላ እየገረመመ ወደቦታው ተመለሰ።

ተፈሪ መኮንን ከነጥላሁን ሰፈር ትንሽ ራቅ ይላል።ያኔ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሌለ ሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ተማሪ ተፈሪ መኮንን ሄዶ መማር ግዴታው ነበር።ከዚያ ግን ፈረንሳይ ለጋሲዮን ላይ ከፍተኛ 12 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገንብቶ ሲጠናቀቅ ጥላሁን ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርቱን ቀጠለ።ጓደኞቹ የነበሩት እነ አለምነህ ዋሴ ፤ ጋዜጠኛ ሰለሞን ጥኡመ ልሳን እና ሌሎች ግን አንመለስም ብለው እዚያው ተፈሪ መኮንን ቀሩ።እሱ ወደ ከፍተኛ 12 ከተመለሰ በኋላ ተፈሪ መኮንን የቀሩት ጓደኞቹ እነሱ ትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ የሚባል ነገር መጀመሩን አዳንቀው ነገሩት።ሚኒ ሚዲያ ምን እንደሆነ የማያውቀው ጥላሁን ተፈሪ መኮንን ጊቢ በአጥር እየገባ ስለሚኒ ሚዲያ ምንነት ከጓደኞቹ ተረዳ።

ስለ ሚኒሚዲያ ያየውን በልቡ ያኖረው ጥላሁን ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ጓደኞቹ መጥቶ ስለ ሚኒ ሚዲያ ምንነት አስረዳቸው ፤ እነሱም እንዲጀምሩ አነሳሳቸው።ተጀመረ።ያኔ ነው እንግዲህ የብዙ ዘመን የሥራ አጋሩ እና የረዥም ዘመን ጓደኛው ከሆነው አለልኝ መኳንንት ጋር የተገናኙት።እርግጥ ጥላሁን እና አለልኝ አባቶቻቸው ጓደኛ ሲሆኑ እነሱም ቢተዋወቁም ሚኒ ሚዲያ ግን የበለጠ አወዳጃቸው።ሚኒ ሚዲያው ተጀመረ።ሥራቸውም እየተወደደ መጣ።ያኔ ደግሞ ሌላ ታሪክ ተከሰተ።ወቅቱ ኤች አይ ቪ የጀመረበት ጊዜ ነበር።እናም ትምህርቱ ሁሉ ኤች አይ ቪ ምን ያህል ገዳይ እንደሆነ እና መድኃኒት እንደሌለው የሚሰበክበት ወቅት ነበር።በአንድ የተማሪዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅት ላይም ተመሳሳይ መልዕክት ከተላለፈ በኋላ እነ ጥላሁን ድራማ እንዲያቀርቡ ተጋበዙ።

ድራማው መቅረብ ጀመረ።መልዕክታቸውም ኤድስ መድኃኒት አለው የሚል ነበር።መልዕክቱ በቦታው የነበረውን ሰው በሙሉ ክው አደረገ።በኋላ በድራማው መጨረሻ ላይ ግን መድኃኒቱ አንድ ለአንድ መወሰን መሆኑን ሲናገሩ ተመልካቹም መምህራኑም ሌሎችም እነ ጥላሁን መልዕክቱን ያስተላለፉበትን መንገድ አድንቀው እጅግ ሞቅ ያለ ጭብጨባ እና ፉጨት አሰሙ። ይሄኔ የአካባቢው ሕዝብ ሁሉ ልጆቻችንን ምን ሆኑብን ብሎ በድንጋጤ ወደ ትምህርት ቤቱ ጎረፈ።የነጥላሁን ዝናም መናኘቱን ቀጠለ።

እነ ጥላሁን ዘውገ ፤ አለልኝ መኳንንት ፤ አለባቸው ጽጌ እና ሌሎችን የያዘው ስብስብ በኪነት በኩል አልፎ ቀስ በቀስ ወደ ዋና መድረኮች መጓዙን ጀመረ።1985 ላይም የእነ ጥላሁን ተራ ደርሶ እነሱም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የመታየት እድሉን አገኙ።ወቅቱ እነ አለባቸው እና ልመንህ ፤ ደረጄ እና ሀብቴ ፤ እንግዳ ዘርን እና አበበ በለው ፤አስረስ በቀለ እና ሌሎችም ከዋክብት መድረኩን ሁሉ የተቆጣጠሩበት ወቅት ነበር።ስለዚህም ጥላሁን እና አለልኝ በኮሜዲ ዘርፍ ቢመጡ እነዚህን ከዋክብት መብለጥ እንደሚያስቸግራቸው ስላወቁ ጠንከር ያሉ ይዘት ያላቸውን ድራማዎች ይዘው መጡ።ሕዝብ ወደዳቸው።ከዚያ በኋላ ለሁለት አስርተ ዓመታት ገደማ ከሺ በላይ ድራማዎችን ሠሩ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥላሁን 1992 ዓ.ም ላይ ትዳር የመሠረተ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም የ4 ልጆች አባት ነው።ልጆቹ የጥበብ ዝንባሌ እንዳላቸው የሚናገረው ጥላሁን ነገር ግን እሱ ለትምህርት ሥራ ቅድሚያ እንደሚሰጥ ይናገራል።"ልጆቼ እኔን መብለጥ አለባቸው።ልጆቼ እኔን ከበለጡ አገሪቱ ታተርፋለች።እኔ ከበለጥኳቸው ግን አገሪቱ ቆማለች ማለት ነው" ይላል።

ጥላሁን አሁንም በሥራ ላይ ነው።ከመድረክ አልራቀም።የኛ ሰፈር የተሰኘ ቴአትር ላይ ይተውናል።የ5 ወር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ አዘጋጅቶ እንደጨረሰም ነግሮናል።ከሥራ የተረፈውን ሰት በምን እንደሚያሳልፍ ጠየቅነው።"አሁን አሁን ተውኩ እንጂ ዋና መዋኘት እና ኳስ መጫወት እወዳለሁ።ከዚያ በተጨማሪ ከጓደኞቼ ጋር አብረን ጊዜ እናሳልፋለን።ለቤተሰቤም ጊዜ እሰጣለሁ" ይላል።

### ለሕዝብ የሚያስተላልፈው መልእክት

"ለሁሉም ነገር ሰላም ነው የሚያስፈልገው።እዚሁ ሰፈር ላይ ቀይ ሽብር እየተባለ ሰው ሲገደል አይቻለሁ። ከዚያም በኋላ ብዙ ነገር አይቻለሁ።እኔ ያየሁትን ልጆቼ ባያዩት ደስ ይለኛል።እስካሁንም አገሪቱ እዚህ የደረሰችው በእግዚአብሄር እርዳታ ነው።አሁንም እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቃት" ብሎናል።እኛም አሜን ብለን ከአንጋፋው አርቲስት ጋር የነበረንን ቆይታ በዚሁ ቋጨን።ቸር እንሰንብት።

# ዓለም አቀፍ



## የየመን ተዋጊ ኃይሎች ለሁለት ወራት ተኩስ ለማቆም ተስማሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት በየመን በጦርነት ተሳታፊ የሆኑ ተዋጊዎች ለሁለት ወራት የሚቆይ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ መድረሳቸውን አስታወቀ።

ከእአአ 2016 ወዲህ በመላው የመን ተፈጻሚ የሚሆን የተኩስ አቁም ስምምት ሲደረስ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

የየመኑ የእርስ በእስርስ ጦርነት በአገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ አስከትሏል። ተመድ በዚህ ጦርነት ምክንያት ወደ 400ሺህ የሚጠጉ ሰዎችን ሳይሞቱ አይቀርም ይላል።

ከእነዚህ መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት በረሃብ፣ በመሠረታዊ የሕክምና አገልግሎት እጦት እና በንጹህ ውሃ አቅርቦት እጥረት ለሞት የተዳረጉ ናቸው።

ይህ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል የተባለው የተኩስ አቁም ስምምነት በሳዑዲ መራሹ ኃይል እና በኢራን በሚደገፉት የሁቲ አማጺያን መካከል የተደረሰ ነው።

የተኩስ አቁሙ ስምምነት ተፈጻሚ መሆን የጀመረው በእስልምና እምነት ተከታዮች የረመዳን ጾም ወር በመጀመሪያ ቀን ነው።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በተባበሩት መንግሥታት አደራዳሪነት የተደረሰው የተኩስ አቁም ስምምነት ለየመናውያን እረፍት ነው ብለዋል።

“ይህ መልካም እርምጃ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። የተኩስ አቁም ስምምነቱ መከበር አለበት። ከዚህ በፊት ተናግሬዋለሁ ይህን ጦርነት ማስቆም አለብን።” ብለዋል ባይደን።

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በበኩላቸው የተኩስ አቁም ስምምነቱ በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲደረግ ጠይቀዋል።

የተኩስ አቁም ስምምነቱ ይፋ የተደረገው በሪያድ የሰላም ንግግር ከተደረገ በኋላ ሲሆን፤ የተመድ ልዩ መልዕክተኛ ሃንስ ግሩንበርግ ተዋጊ ኃይሎች የአየር፣ የመድር እና የባህር ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በየመን እና በድንበር አካባቢዎች ለማቆም ተስማምተዋል ብለዋል።

መርከቦች በሁቲ አማጺያን ቁጥጥር ሥር ወደምትገኝ አል-ሁዳይዳህ ወደብ መግባት እንዲችሉ እንዲሁም የመንገደኞች አውሮፕላን በሁቲ አማጺያን ስር በምትገኘው የየመን መዲና ሰነዓ እንዲያርፉ የተኩስ አቁም ስምምነቱ ላይ ተመልክቷል።

ሳዑዲ መራሹ ኃይል የየመን ይፋዊ መንግሥት በመደገፍ ከሁቲ አማጺያን ጋር ባለፉት 7 ዓመታት ሲዋጋ ቆይቷል።

የሁቲ አማጺያን በበኩላቸው ሰው አልባ አውሮፕላኖችን እና ሚሳኤሎችን በመጠቀም ሳዑዲ አረቢያን እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶችን ሲያጠቁ ቆይተዋል።



## የጋዝ ክፍያ በሩብል እንዲሆን የጠየቀችው ሞስኮ የጋዝ አቅርቦት አይቋረጥም አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ለአውሮፓ ኅብረት የምትልከውን ጋዝ እንደማታቋርጥ ብታስታውቅም አገራቱ ግን ለሚገዙት የጋዝ ምርት ክፍያቸውን በሩብል እንዲፈጽሙ መጠየቋ አከራካሪ ሆኗል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከዓርብ ዕለት ጀምሮ የሞስኮን ጋዝ የሚገዙ የሩሲያውን መገበያያ ሩብል በመጠቀም በሩሲያ ባንኮች አማካይነት ክፍያ እንዲፈጽሙ አዘዋል።

ክሬምሊን እንዳስታወቀው ቀድሞ ክፍያ የተፈጸመባቸው ግዢዎች ይህ ሕግ እንደማይመለከታቸው እና ከያዝነው የፈረንጆቹ አዲስ ወር መጀመሪያ እስከ አጋማሽ ድረስ ወደ ገዢዎች እንደሚላኩ አስታውቋል።

የምዕራቡ ዓለም አገራት ሩሲያ ላይ የጣሉትን ማዕቀቦች ተከትሎ ነው ሩሲያ መገበያያ ገንዘቧን ለማጠናከር መሰል እርምጃዎችን ለመከተል የተገደደችው።

ክፍያዎቹ በሩብል ስለመፈጸማቸው ማረጋገጫ ካልተገኘ የጋዝ አቅርቦቱን ሩሲያ ታቋርጣለች ማለት ግን አይደለም ሲሉ የክሬምሊን ቃል አቀባዩ ዲሜትሪ ፔስኮቭ።

የአውሮፓ ኅብረት በበኩሉ ይህንን የሩሲያ ውሳኔ ተከትሎ የኃይል አቅርቦት ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች ክፍያ እንዴት ሊፈጸም እንደሚቻል እያነጋገር መሆኑን አስታውቋል።

የኅብረቱ የኃይል ዳይሬክተር የሆኑት ዲቴ ዩል ዮርገንሰን በትዊተር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹የአውሮፓ ኅብረት ከአባል አገራትና ወሳኝ ዘርፎች ጋር በቅርበት እየሠራ ነው። ለሩሲያ የሚፈጸሙ ክፍያዎች በምን አይነት ገንዘብ እንደሚከናወኑ መግባቢያ አማራጮችን እየፈለግን ነው›› ብለዋል።

ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረች በኋላ የምዕራቡ ዓለም አገራት በርካታ የሩሲያ መንግሥት ላይ፣ የሩሲያ ድርጅቶች እና ባለሃብቶች ላይ ማዕቀብ ጥለዋል።

በሌላ በኩል ከአሜሪካ እና ካናዳ በተለየ መልኩ የአውሮፓ ኅብረት በሩሲያ ጋዝ ግዢ ላይ ማዕቀብ መጣል አልቻለም።

ምክንያቱ ደግሞ 40 በመቶ የሚሆነውን የአውሮፓ ኅብረት የጋዝ ፍላጎት የምታቀርበው ሩሲያ ናት።

ከዚህ በፊት በነበሩት የንግድ እንቅስቃሴዎች መሠረት የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ክፍያ የሚፈጽሙት በዩሮ እና በዶላር ነበር።

የአውሮፓ ኅብረት አባላት አገራት የሩሲያ የጋዝ አቅርቦት ቢቋረጥ ሌላ አማራጭ ማግኘት ቀላል አይሆንላቸውም። ሩሲያ በየዕለቱ ለኅብረቱ ጋዝ እየሸጠች 400 ሚሊዮን ዩሮ ትሰበስባለች።

ሩሲያ ምናልባት የጋዝ አቅርቦቷን ልታቋርጥ ትችላለች የሚል ስጋት የገባቸው የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ሁኔታውን በቅርበትና በጭንቀት እየተከታተሉት ነው።

ረቡዕ ዕለት ጀርመን እና ኦስትሪያ የተመጠነ ጋዝ ለዜጎቻቸው ማከፋፈል ጀምረዋል። የጀርመን መንግሥት ተጠቃሚዎችና ድርጅቶች በተቻላቸው መጠን የጋዝ አጠቃቀማቸውን እንዲከታተሉና እንዲቀንሱ ጠይቋል። ኦስትሪያ በበኩሏ የጋዝ ገበያው ወዴት እያመራ ነው የሚለውን እየተከታተለችውን እንደሆነ አስታውቃለች።


## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ሰዎች ለሰዎች ድርጅት በሶማሊያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፋፈን ዞን ሀሮሪሳ ወረዳ ለሚገኙ ተረጂዎች አገልግሎት የሚውል

1ኛ አንደኛ ደረጃ የስንዴ ዱቄት 3,000 ኩንታል

2ኛ ፈሳሽ የምግብ ዘይት 10,000 ሊትር

3ኛ አንደኛ ደረጃ ሩዝ 2,000 ኩንታል

በዘርፉ ከተሰማሩ ህጋዊ ድርጅቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል :: ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለፁትን መስፈርቶች የምታሟሉ እንድትጫረቱ ተጋብዛችኋል፡፡

ተጫራቾች ማሟላት የሚገባቸው፤

1. በዘርፉ የተሰማሩበት ለ2014 ዓ.ም የታደሰ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ፤
2. የንግድ ምዝገባና ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፤
4. የግብር ከፋይ ምዝገባ (TIN Number) ማቅረብ የሚችል ፤
5. የዘመኑን ግብር የከፈሉ /ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጨረታ ለመሳተፍ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
6. ተወካይ ከሆነ/ች ህጋዊ የውክልና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል/የምትችል ፤
7. ተጫራቾች በዋጋ ማቅረቢያ ሰነዳቸው ላይ የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤
8. ዋጋ በሚሞሉበት ጊዜ የአንዱን ኩንታልና የአንዱን ሊትር በትክክል መሞላት አለበት፤
9. ተጫራቾች የአንዱን ዋጋ ከሞሉ በኋላ የጠቅላላ ድምር ወደ ጎንም ወደ ታችም ደምረው ማስቀመጥ አለባቸው ፤
10. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው በተቀመጠው የዕቃ ዝርዝር በተናጥል ለእያንዳንዱ ዕቃ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ይሆናል፤
11. በጨረታ ሰነዱ ላይ ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም፤
12. ተጫራቾች የራሳቸውን የዋጋ ማቅረቢያ (Proforma Invoice) ሰነድ ሲያቀርቡ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ማያያዝ ግዴታ ነው፡፡
13. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ባቀረቡት ዋጋ ልክ 2% በጥሬ ገንዘብ በCPO ማስያዝ የሚችል መሆን አለበት ፤
14. ተጫራቾች በሚሰጡት ዋጋ ላይ የትራንስፖርት ሂሳብ ማስገባት አለባቸው። እህሉ ከሚገኝበት መጋዘን እስከ ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋፈን ዞን ሀሮሪሳ ወረዳ ድረስ ከጅጅጋ ከተማ 40 ኪ.ሜትር ላይ ይገኛል፡፡ የሚቀርበው የጭነት ተሽከርካሪ ቢያንስ 400 ኩንታል የሚጭንና ከዛ በላይ መሆን አለበት፡፡
15. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያውን ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7(ሰባት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
16. ሰባተኛው ቀን ቅዳሜ/እሁድ ላይ ከዋለ በቀጣይ የሥራ ቀን ይሆናል፡፡
17. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለሰባት ቀን ይቆይና በሰባተኛው ቀን ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ ከቀኑ 8፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች በተገኙበት በሰዎች ለሰዎች ድርጅት ዋና መ/ቤት ቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ቀይ አፈር አካባቢ በድርጅቱ አዳራሽ ይከፈታል፡፡
18. አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች ድርጅቱ በሚሰጠው የአቅርቦት ትዕዛዝ መሠረት ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ዕቃውን አሟልቶ ማቅረብ የሚችልና በድርጅቱ ተረጋግጦ ካልተቀበለው ቀይሮ የማምጣት ግዴታ አለበት፡፡
19. አሸናፊ የሆነው አቅራቢ ክፍያ በሚጠይቅበት ጊዜ ህጋዊ ደረሰኝ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህንን ማቅረብ የማይችል ከሆነ ምንም አይነት ክፍያ መጠየቅ አይችልም፡፡ መ/ቤቱም እንዲከፍል አይገደድም፡፡
20. በዚህ ማስታወቂያ ያልተገለፁ ሌሎች ህጎች በሀገሪቱ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡
21. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ Menschen fur Menschen ስም አዘጋጅተው በፖስታ በማሸግ ከዋጋ ማቅረቢያው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
22. የጨረታው ውጤት ጨረታው ተገምግሞ እንዳለቀ በደብዳቤ ወይም በውስጥ ማስታወቂያ የሚገለፅ ይሆናል፡፡
23. ተጫራቾች አሸናፊ ከሆኑ ላሸነፉበት ጠቅላላ ዋጋ 2% የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና (ውል ማስከበሪያ) በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
24. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
25. ተጫራቾች ሌላ ተጫራች በሰጠው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መስጠት አይችሉም፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር 0114 71 42 91 / 0114 71 43 58 በሥራ ሰዓት ደውሉ ማግኘት ይቻላል፡፡

## ሰዎች ለሰዎች ድርጅት




# ስለ ሰላም ከሕፃን አርሴማ አንደበት

አሥመረት ብሥራት

**ለሰው ልጆች ፍቅር ለሰው ልጆች ሰላም**
**ለሰው ልጆች ፍቅር ለሰው ልጆች ሰላም**
**ለሰው ልጆች በዓለም ዙሪያ ሁሉ**
**ሰላም ይሁን ምድሩ ሁሉ**
**ሕፃናት እንዲያድጉ በንፁሕ አዕምሮ**
**ነፃ ሕሊናቸው ጎልብቶና ዳብሮ**
**ወጣት ሽማግሌ የሰው ዘር ሁሉ**
**ሰላም ለዓለማችን ይላሉ በሙሉ።**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ሰላም ነው? ትምህርታችሁን በደንብ እየጎበዛችሁ ነው አይደለ፤ ጎበዞች ሁኑ እሺ። ለዛሬ በጣም ጎበዝ ሠዓሊ የሆነችውን አርሴማ ጌትነትን ላስተዋውቃችሁ። አርሴማ ስምንት ዓመቷ ሲሆን መፃፍ ከቻለችበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ሥዕሎችን መሳል እንደጀመረች ትናገራለች። የሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው አርሴማ ሥዕል አስተማሪዎቿ የሳሉትን ከመድገም አንስቶ የተለያዩ ሥዕሎችን በራሷ መንገድ እየሳለች የምታስቀምጥ ሲሆን በሥዕሎቿ ሀሳቧ ውስጥ ያለውን በሙሉ ለመግለፅ እንደምትሞክር ትናገራለች። በትምህርቷ በጣም ጎበዝ ልጅ የሆነችው ተማሪ አርሴማ እሷ ሰላም ያለበት ቦታ በመኖሯ ትምህርቷን በደንብ መማር፣ ሥዕለ መሳል እንደፈለገች መጫወት መቻሏ ቢያስደስታትም ሌሎች ጦርነት አካባቢ ያሉ ልጆች ግን ይህን እድል ያለማግኘታቸው እንደሚያሳዝናት ተናገራለች።

"እኛ ልጆች ሰላም ያስፈልገናል። እኛ የምንኖርበት ቦታ ሰላም ቢሆንም ጦርነት አካባቢ ያሉ ልጆች እየራባቸው፤ እየሞቱ ያሉ ልጆች በሰላም እንዲኖሩ ትልልቅ ሰዎች እባካችሁ መጣላት ተዉ፤ ሰላም ይሁን" ትላለች።

በቴሌቪዥን የሚታዩት ነገሮች ሁሉ እንደሚያስጨንቋት የምትናገረው አርሴማ በእሷ አንደበት ይህን ያህል መናገርዋ ቢያሳዝንም "እባካችሁ የፈጠርናቸውን ልጆች ዓለማቸውን አናጨልምባቸው፤ በቃ በሉና ሰላም ይሁን" ትላለች።

የሰላም ዋጋውን የሚረዳው ጦርነት ውስጥ ያለፈ ነውና ዋጋው ምን ያህል ውድ እንደሆነ ተረድተን ከጠፋው ጥፋት በላይ ሌላ እንዳይጨመር ዛሬ ላይ ልናቆም ይገባል በሚል የሕፃን አርሴማን ሀሳብ ተጋርቼ አበቃሁ።



# ስፖርት






## የኳታሩ ዓለም ዋንጫና የምድብ ድልድሉ

ብርሃን ፈይሳ

በታላቋ አህጉር እስያ ለሁለተኛ ጊዜ፤ በዓረቡ ዓለም ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው የኳታር ዓለም ዋንጫ ሊካሄድ ወራት ብቻ ቀርተዋል። በዚህ የምድራችን ትልቁ የእግር ኳስ ውድድር ላይም ተሳታፊ ከሚሆኑት 32 አገራት መካከል 29ኙ ተለይተዋል፤ የምድብ ድልድሉ ከትናንት በስቲያ ምሽት ታውቋል። የውድድሩ ባለቤት የሆነው ፊፋ ከአዘጋጅነት ምርጫው ጋር በረሃ ላይ የተመሰረተችው ዘመናዊቷ ሃገር ኳታር ደግሞ ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ጋር በተያያዘ በርካታ ቅሬታዎች ሲነሱባቸው የቆየ ይሁን እንጂ፤ ለተቺዎቻቸው ጆሮ ባለመስጠት ዝግጅቱ ተጠናቆ የውድድሩ መጀመር በጉጉት እየተጠበቀ ይገኛል።

የውድድሩ መጫወቻ ኳስ ከሰሞኑ ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ ግዙፉ የስፖርት ትጥቅ አምራቹ አዲዳስ ያዘጋጀው መሆኑ ታውቋል። ከሰሞኑ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው ኳስ ‹‹አል ሪሃላ›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፤ የዓረቦች ባህላዊ ልብስ የሆነው ነጭ ቀለም ከኳታር ባንዲራ ጋር ባጣመረ ቀለም የተዘጋጀም ነው። ‹‹ስፒድሼል›› የተባለ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ የተደረገበት መሆኑ የተነገረለት ኳሱ፤ ከፍተኛ ፍጥነትና የመተታጠፍ አቅም ያለው መሆኑ ታውቋል።

ዓለም ዋንጫው 32 አገራትን የማሳተፍ ምዕራፉ በዚህ ውድድር የሚዘጋ ሲሆን፤ ከአራት ዓመታት በኋላ በሚካሄደው ውድድር 48 አገራትን ለመጀመሪያ ጊዜ ይካፈላሉ። ይኸውም ባልተጠበቀና በአሳዛኝ ሁኔታ ከዓለም ዋንጫ ለሚቀሩ አገራት ተስፋን የሚያለመልም ሆኗል። ከሰሞኑ ተጠቃለው የታወቁት የውድድሩ



| Group A | Group B | Group C | Group D |
|---|---|---|---|
| Qatar | England | Argentina | France |
| Ecuador | IR Iran | Saudi Arabia | IC Play-off 1 |
| Senegal | USA | Mexico | Denmark |
| Netherlands | Euro Play-off | Poland | Tunisia |

| Group E | Group F | Group G | Group H |
|---|---|---|---|
| Spain | Belgium | Brazil | Portugal |
| IC Play-off 2 | Canada | Serbia | Ghana |
| Germany | Morocco | Switzerland | Uruguay |
| Japan | Croatia | Cameroon | Korea Republic |

ተሳታፊ አገራት ባሻገር አስደናቂ በሆነ መልኩ በመድረኩ የማይታዩ ቡድኖች ጉዳይ አነጋጋሪ ነበር። የአውሮፓ ዋንጫ አሸናፊዋና ዓለም ዋንጫን ለአራት ጊዜያት ያነሳችው ጣሊያን የዓለም ዋንጫ ተካፋይነት ጉዞዋ በማጣሪያው ተገቷል። ከዓለም ዋንጫው ስትርቅም ይህ ሁለተኛ ጊዜዋ ነው። ያለፈው የዓለም ዋንጫ አዘጋጅ የነበረችው ሩሲያ ደግሞ ከዩክሬን ጋር በገባችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ምክንያት ከየትኛውም ውድድር የተገለለች አገር መሆኗ ይታወሳል።

በአምስት አገራት የምትወከለው አፍሪካ፤ ሴኔጋል፣ ጋና፣ ቱኒዚያ፣ ሞሮኮ እና ካሜሮን በዓለም ዋንጫው ተሳታፊ የሚያደርጋቸውን ትኬት መቁረጣቸውን እርግጠኛ ሆነዋል። በአህጉሪቱ የእግር ኳስ ችሎታቸው የተሻሉ የሚባሉት እንደ ግብጽ፣ ኮትዲቯር፣ ናይጄሪያ እና አልጄሪያ ያሉት አገራት አለማለፋቸው በእግር ኳስ ቤተሰቡ አስገራሚ ጉዳይ ነበር። ከሶስት ቡድኖች በቀር (ቡድኖቹ ባይታወቁም በምድብ 2፣ 4 እና 5 ተደልድለዋል) አብዛኛዎቹ ተሳታፊ አገራት መለየታቸውን ተከትሎም በተካሄደው የምድብ ድልድል አዘጋጇ አገር ኳታር በምድብ አንድ ከኢኳዶር ጋር የመክፈቻውን ጨዋታ እንደምታደርግ ታውቋል። ሴኔጋልና ሆላንድም በዚሁ ምድብ ተጠቃለዋል።

በምድብ ሁለት እንግሊዝ፣ ኢራን እና አሜሪካ ሲደለደሉ፤ በቀጣይ ከዩክሬን፣ ስኮትላንድ እና ዌልስ አሸናፊ የሚሆነው ቡድን ምድቡን ይቀላቀላል። የሁለት ጊዜ የዓለም ዋንጫ ቻምፒዮናዋ የሜሲ አገር አርጀንቲና ከሳዑዲ ዓረቢያ፣ ሜክሲኮ እና ፖላንድ ጋር በምድብ ሶስት ተገኝተዋል። ያለፈውን የዓለም ዋንጫ ለሁለተኛ ጊዜ ያነሳችው ፈረንሳይ ደግሞ ከዴንማርክ፣ ቱኒዚያ እንዲሁም እስካሁን ካልታወቀው ቡድን ጋር ተመድባለች። ምድብ አምስት የአራት ጊዜ ዓለም ዋንጫ ባለቤቷ ጀርመንን፣ ከስፔን፣ ጃፓን እና በቀጣይ ከሚታወቀው ቡድን ጋር አገናኝቷታል። በምድብ ስድስት ቤልጂየም፤ ከካናዳ፣ ሞሮኮ እና ክሮሺያ ጋር ተደልድላለች። የዓለም ዋንጫን ለአምስት ጊዜያት በመውሰድ አቻ ያልተገኘላት ብራዚል፤ በምድብ ሰባት ከሰርቢያ፣ ስዊዘርላንድ እና ካሜሮን ጋር ተሰልፋለች። የመጨረሻው ምድብ ላይ የሚገኙት አገራት ደግሞ ፖርቹጋል፣ ጋና፣ ኡራጓይ እና ደቡብ ኮሪያ መሆናቸው ታውቋል።

በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ለሚካሄደው ውድድር ኳታር ዝግጅቷን አጠናቃለች። ውድድሩ በሚካሄድበት ወቅት በሌላው ዓለም ክረምት ይሁን እንጂ በኳታር ያለው ሙቀት አስቸጋሪ እንደሚሆን ከወዲሁ ይጠበቃል። ነገር ግን አገሪቷ ያዘጋጀቻቸው ስምንት ግዙፍ ስታዲየሞች እጅግ ዘመናዊና የአየር ሁኔታውንም መቆጣጠር የሚችል ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው መሆኑን በተደጋጋሚ አሳውቃለች። 28ቀናትን በሚቆየው ውድድር ላይም 1ነጥብ5 ሚሊዮን የሚሆኑ ደጋፊዎች ይካፈላሉ በሚል ሲጠበቅ፤ ቁጥራቸው ከዚህ የሚልቁት ደግሞ ማረፊያቸውን በተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ አድርገው በ70 ደቂቃ የአየር በረራ ብቻ ጨዋታዎችን መመልከት እንደሚችሉም ተጠቁሟል።